# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

የቲዎሪ መጽሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተዘጋጀ

ሰኔ 1962

# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

የቲዎሪ መጽሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተዘጋጀ

አዘጋጅ፦ ነገደ ጎበዜ

ዋጋው አንድ ብር

ሰኔ 1962

| ይዘት | ገጽ |
| --- | --- |
| ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ እንዘጋጅ | 1 |
| ግልፅ ደብዳቤ ለአጉል ገለልተኛ | 1 |
| የኢምፔሪያሊስት ብዝበዛ | 17 |
| እድገትና የእድገት ችግሮች | 30 |

## ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ እንደራጅ

« . . . ለብዙ አመታት ታዛቢዎች ከንጉሰ ነገስቱ በኋላ በኢትዮጵያ ላይ የገሃነም እሳት ይወርዳል ሲሉ ነበር።አሁን ግን እንደዚህ አይነቱ መአት ንጉሰ ነገስቱ እስኪያልፍም የሚጠብቅ አይመስልም የኢትዮጵያ እልቂት ከኮንጎ፣ከቢያፍራና ከሱዳን ይበልጥ አሰቃቂ ይሆናል።በኢትዮጵያ ውስጥ እስላሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ጨካኝ ጦረኞች ናችው።ይህ በዘመናዊ መሳርያ የሚያደርጉት ሪቮሉሽን ወይም ደግሞ የእርስ በእርስ ፍጅት አስደናቂውን "የኢትዮጵያ ታሪክ" ከፍፃሜ ያደርሰዋል »(1)

እንደዚህ አይነቱ አነጋገር፣ታዛቢ ነኝ የሚል ሁሉ ስለኢትዮጵያ የሚያቀርበውን ስሁፍ የሚደመድምበት አቡነዘበሰማያት ሆኗል ስለኢትዮጵያ ዕጩ ከሀይለስላሴ በኋላ ታሪኳ ይደመሰሳል፣ኢትዮጵያ ትጠፋለች፣ህዝብዋ ይተላለቃል በማለት የሽብር ቃሉን ሳይሰነዝር ብእሩን የሚያስቀምጥ ታዛቢ እየጠፋ ሄዷል።

እርግጥ ሥጪው ጊዜ ታላቅ የለውጥና የትርምስ አውሎ ነፋስ ያዘለ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።በታሪካችን እንደምናየው የበዝባዦች "በውርስ ዘመን" ጊዜ መተረማመስ የተለመደ ነው።ዛሬ ግን ይህንም የሚያባብሱና ልዩ መልክ የሚሰጡ ልዩ አዳዲስ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።የኢትዮጵያ ህዝብ እያደር እየጠነከረ በሚሄደው ጭቆና በመመረር በያለበት በበለጠ በመነሳሳት ላይ ነው።የባእድ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት ከመቸውም ይበልጥ በሀገራችን ስር ሰዶ ሀገራችንን ጥገኛ ስላደረጋት አገር ወዳድ ሁሉ ማጉረምረም ጀምሮአል።

ለዚህ ለማይቀረው ተጋድሎ ሁሉም እንደመሰለው በመደራጀት ላይ ነው።ገገርዎቻችን በዘረፋው ድርሻ አለመስማማት ለሚመጣው ጭቅጭቅም ሆነ ወይም በፀረ ህዝብ አንድነታቸው ለመደላደል ውስጥ ውስጡን በመደራጀት ላይ ናቸው።የኢትዮጵያ ህዝብ በዝባዦቹ እንደዚህ ከዘረጉለት ወጥመድ ውስጥ ከገባ እውነትም አሰቃቂና ከ

(1) ቁጥር ለተደረገባቸው ሁሉ በፅሁፉ መጨረሻ ማብራሪያ ይሰጣል

ንቱ፡ ደም መፋሰስ ይመጣል።የኛ አላማ ይህ የማይቀር ትንንቅ መስመር
ይያዝ የሚል ነው፣እንደሚይዝም ሙሉ ተስፋ አለን።ተበዝባጋዥ በበዝ
ባዥ ላይ እጁን እንዲያነሳ፣ለነፃነት ትግላችን ሊውል የሚገባው ሀይል
በከንቱ ትርምስ የትም ባክኖ እንዳይቀርና የነፃነት ትግላችን ከሚገባው
በላይ እንዳይራዘም የሚያስፈልገው ከአሁኑ የተበዝባዡ ህዝብ በሙሉ
በአንድ ግልፅ በሆነ ፕሮግራምና የስራ ውጥን አማካኝነት መደራጀት ነ
ው።ለዚህም ሰላምን፣ነፃነትን፣እርምጃንና አገሩን ወዳድ የሆነ ኢትዮጵያ
ዊ ሁሉ የማይቆጠብ ጥረቱን ማበርከት አለበት።

መጭውን ጊዜ ታላቅ የትግል ማእበል ያዘለ የሚያደርገው
ምንድነው? ለኢትዮጵያ ህዝብ ሰላም፣ነፃነት፣እርምጃና ብልፅግና የምንቆ
ረቆር ኢትዮጵያዊያን ተግባራችን ምንድን ነው? እነዚህን ጥያቄዎች በ
መጠኑ ለመመለስ እንሞክራለን።ሀሳባችን በዚህ ታላቅ ጉዳይ ላይ መሰ
ረታዊ የሆኑ አንዳንድ አስተያየቶች ለመሰንዘርና ውይይት ለመክፈት
እንጂ ለእንደዚህ አይነቱ ሰፊ ጉዳይ የተሟላ መልስ ለመስጠት አይ
ደለም።

## I

መጪው ጊዜ የትግልና የትርምስ መሆኑን ለመረዳት ያለ
ፈውን ታሪካችንን፣የዛሬውን የሃገራችንና የአለምን ሁኔታ መመልከት
ያስፈል ጋል።

በታሪካችን "የውርስ ጊዜ" የስልጣን ትግልና ታላላቆች ባ
ላባቶች ለጥቅም ሽሚያቸው ሲሉ ህዝቡን በዚህ ቅደም በዚያ ተሰለፍ እ
ያሉ የሚያፋጁበት የትርምስ ወቅት ነው።ሪቻርድ ግሪንፊልድ በዚህ ጉ
ዳይ ሲፅፍ «የኢትዮጵያ ታሪክ በግልፅ እንደሚያሳየን ዘውድን ለመቀ
ዳጀት ከንጉስ መወለድ ብቻ፣ምንጊዜም በቂ ሆኖ አያውቅም።እስከዛሬም
ቢሆን ሀይለኛ ባላባቶች (እንደልማድ አድርገውት) በውርሱ ላይ ለማ
ደምና ስልጣን ለመሻማት አመንትተው አያውቁም» (2) በማለት አት
ቷል።

ያለፉትን የመቶ አመታት ታሪካችንን ዘወር ብሎ ማየት ብቻ
ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው።የቴዎድሮስ ሞት ከስከተለው ትርምስ በኋላ የ
ጊዜው ባለሀይል ዋግሹም ጉበዜ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ዙፋኑን



ይዘው ነበር።ይበልጥ የደረጀ ሃይል ያጠራቀሙት ደጃች ካሳ በሶስት አ
መት ውስጥ ተክለ ጊዮርጊስን ከአልጋ አውርደው አፄ ዮሀንስ ተባሉ።
አፄ ዮሀንስ መተማ ሲወድቁ ዙፋኑን ለልጃቸው ለራስ መንገሻ "ቢናዘዙ
ም" የንጉሰ ነገስቱ ዘውድ ለጊዜው ባለሀይል፣ለሸዋው ምኒልክ ሄደ።ከአ
ፄ ምኒልክ በኋላ የልጅ እያሱን፣የኢቴጌ ጣይቱንና የራስ ተፈሪን የስል
ጣን ትንንቅና ያስከተለውን ትርምስ ሁላችንም የምናውቀው ነው።ይህ
ን ሁሉ ማለታችን አጥንት ቆጠራውን እስከዚህም ዋጋ ሰጥተነው አይደ
ለም።ታሪክን በሬ ወለደ እያሰኙ ዘውድ የሰላምና የአንድነታችን ዋስት
ና ነው ለሚሉ ሁሉ፣እንዲያውም "የውርስ ጊዜ" የትግል፣የፍጅትና የት
ርምስ ወቅት መሆኑን ለማስታወስና አሁንም ጨቋኞች እንደለመዱት
ለጥቅም ሲታገሉ ህዝባችንን እርስ በእርሱ እንዳያፋጁት ከታሪክ እን
ማር ለማለት ነው።

ከዚህም በላይ "መጪው ጊዜ የትግል ማእበል አዝሏል" ለ
ማለት የሚያስችለን ምርኩዛችን የጊዜው የኢትዮጵያና የአለም ሁኔታ
ነው።ዛሬ በኢትዮጵያ ሁለት ጉልህ ነገሮች እናያለን።መጀመሪያ ነገር በ
ህዝቡና በታላላቅ ባላባት መካከል ያለው ጠብ እየከረረ ሄዷል።ስለዚህ
ም በአለፉት አመታት በያለበት የተጀመሩት ትግሎች እየተፋፋሙ ሄ
ደዋል።ሁለተኛ ደግሞ በአገራችን ጉዳይ ከመቸውም ይበልጥ ኢምፔሪ
ያሊስቶች ጣልቃ ሲገቡ እናያለን።የኢምፔሪያሊስቶችን ጉዳይ በሃገራ
ችን ወስነን ልናየው አንችልም።በአፍሪቃ፣በእስያና በላቲን አሜሪካ ፀረ
ኢምፔሪያሊስት ህዝቦች ተነስተው በመታገል ላይ ናቸው።ይህ በኢም
ፔሪያሊዝምና በአለም ተበዝባዥ ህዝቦች መካከል የሚደገረው ትግል
ለዘመኑ መልክ ከሚሰጡት ገድሎች ዋናው ነው ብለን እናምናለን።መ
ጪው ጊዜም በአለም (በሃገራችንም) ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆነው ት
ግል እየበረታ የሚሄድበት መሆኑን መረዳት አዳጋች ነገር አይደለም።

በባላባቶቹ መንግስትና በህዝብ መካከል ያለው ጠብና መቆ
ራረጥ እየከረረ ሄዷል።በየጊዜው እንደምናያቸው የባላባቶቹ መንግስ
ት እንኳንስ ተገቢ የሆኑትን የህዝብ መሰረታዊ ፍላጐቶች ለማርካትና
ቆሞ ለመሄድ እንኳን ህዝቡን በይበልጥ ለመዝረፍና ለመጨቆን ተገዷ
ል።ይህም ስርአት እስከተሻረ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ እድል እርምጃና

ብልፅግና ሳይሆን ይበልጥ መራቆትና መጨቆን መሆኑን በፍፁም አን ጠራጠርም።ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ የባላባቶቹን ጭቆና ለመቋቋ ም ይነሳል።ተነስቷልም።ይህን ስንል በከንቱ ምኞት ላይ በተመሰረተ ቅ ዠት ተመርተን አይደለም።የኢትዮጵያ ህዝብ የባላባቶቹንና የኢምፔሪ ያሊስቶችን ዘረፋ ተቋቁሞ የደህንነቱን መንገድ በትግሉ ለመትለም የ ሚነሳው እየተባባሰ የሚሄደው ጭቆና ስለሚያስመርረውና ሌላ ምርጫ በመንሳት ለቆራጥ ትግል ስለሚገፋፋው ነው።ነገር ግን በጭቆና ተመርሮ መነሳት ብቻ የእውነተኛ ነፃነት ዋስትና ሊሆን አይችልም።በሌላው አፍ ሪቃና ሩቅም ሳንሄድ በገዛ ሃገራችን እንደምናየው የህዝቡን ሀይል ለ ማባከን፣አንድነቱን ለመስበርና ጥቅማቸውን ለመጠበቅም ሆነ ለማደር ጀት በዝባገሮች ህዝቡን በነገድና በሀይማኖት እያለያዩ ሊያፋጁት ይች ላሉ።ለዚህም የተከማቸው የህዝብ ቁጣና ሀይል ለዋናው የነፃነት ትግል ሳይውል ለብዙ ጊዜ በነገድና በሀይማኖት ትርምስ የትም በከኖ እንዳይ ቀር መጠንቀቅም ያስፈልጋል።

ሁለተኛ ደግሞ የጊዜው የአለም ሁኔታ አለ።ኢትዮጵያችን እንደቀድሞው "በራሳቸው አለም ተረስታ" አልተኛችም።በተለይ ያለፉ ት መቶ አመታት ታሪካችን ደግሞ እንዳሳየን በሃገሪቱ ውስጥ የሚደረ ገው የስልጣንና የጥቅም ትግል የውጭ ዘራፊዎችም እንደየጥቅማቸው ጣልቃ እየገቡ የሚፈተፍቱበት ግርግር ነው።አፄ ዮሃንስ ዙፋኑን ለመ ያዝ የተገለገሉበትን ብዙ መሳርያ ለማከማቸት የቻሉት በአፄ ቴዎድሮ ስ ላይ በተደረገው ዘመቻ ከእንግሊዞች ጋር በመተባበራቸው ነበር።አፄ ምኒልክ ዘውዱን ለመቀዳጀት ከኢጣልያኖች ብዙ የገንዘብና የመሳሪያ እርዳታ ማግኘታቸውን ታሪክ ይመሰክራል።በልጅ እያሱና በራስ ተፈሪ መካከል ትንንቁ ሲካሄድ ፈረንሳይ፣እንግሊዝና ጣልያን ራስ ተፈሪን ሲ ያግዙ ጀርመንና ቱርክ ደግሞ ወደልጅ እያሱ ያዘነበሉ እንደነበረ ይታ ወሳል።አፄ ምኒልክ አርጅተው የውርሳቸው "ጣጣ" የጊዜውን ኢምፔሪ ያሊስቶች በጣም አስግቷቸው በነበረ ጊዜ የኤሪትራ ገዢ የነበረው ሲኞ ር ማርቲኒ የኢምፔሪያሊስቶችን ጣልቃ ገብነት ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሏ ል።«በኢትዮጵያ መጭው ጊዜ በጣም አጠራጣሪ በመሆኑና አፄ ምኒልክ ም እያረጁ በመሄዳቸው ታላቋ ብሪታኒያ፣ኢጣልያንና ፈረንሳይ በአንድ



ነት ሆነው ከቀረቡት ወራሾች ሁሉ የትኛውን እንደሚደገፉና ከስፈለገ ም የትኛውን የግድ እንደሚያነግሱ ከአሁኑ መስማማት ይገባቸዋል።በ ዚህ ጉዳይ ምንም አይነት ክርክርም ሆነ የሃሳብ ልዩነት ሊኖር አይገባ ም»።(3) ይህ የተነገረው የዛሬ ሃምሳ አመት ነው!

ከዛሬ ሃምሳ አመት ይልቅ ዛሬ በሀገራችን ኢምፔሪያሊስቶ ች ይበልጥ እጃቸውን ያስገቡ መሆናቸውን ለማስረዳት ብዙ መዘብዘብ አያስፈልገንም።ዛሬ በሀገራችን የገነነው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የ መከላከያ ሀይላችንን፣ትምህርታችንን፣የኢኮኖሚያችንን ቁልፎች በእጁ ጨብጦ እንደያዘ ሁሉ ያውቃል።ነገ ከላይ ከሚፋጩት ሀይሎች ለጊዜ ው ገናና የሚሆነው የአሜሪካኖችን ድጋፍ የሚያገኘው አድሃሪ ሀይል መሆኑ አይከድም።ለዚህም የሚደረገው ዝግጅት የአደባባይ ምስጢር ሆ ኗል።በቅርቡ ሮጀርስ የተባለው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወደ አዲስ አበባ በመጣበት ወቅት "ለ ሞንድ" የተባለው ጋዜጣ ሲፅፍ እንዲ ህ ብሏል።«አፍሪቃን በሚዞርበት ጊዜ ሚስተር ሮጀርስ ዋሽንግተንን በ ሚያሳስቡ ሁለት ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ይችላል።ይኸውም እያረጁ የ ሄዱት የሀይለስላሴና የጆሞ ኬንያታ ውርስ ጉዳይ ነው . . . በተለይ የኢ ትዮጵያ ጉዳይ የአሜሪካን መሪዎች በጣም የሚያሳስባቸው ነው . . .»(4)

ከዚህ በፊት እንደተባለው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ጥ ቅማቸውን የሚጠብቅላቸው ከሆነ ወልደ ጊዮርጊስን ሆነ ወልደ ገብር ኤልን ቢደገፉ ግድ የላቸውም።ነገር ግን አሜሪካኖች ስለደገፉት ብቻ በ ኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተወዝፎ ብዝበዛውን የሚቀጥል መንግስት በኢት ዮጵያ ውስጥ ሊኖር አይችልም።ከግማሽ ሚልዮን በላይ የሚሆኑ የአሜ ሪካና የጥገኞቹ ወታደሮች ዘምተውበት በጀግንነት የተቋቋማቸው የቬ ትናም ህዝብ ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው።ለኢትዮጵያ ህዝብ ከውጭ የመ ጣን ጠላት መቋቋም ደግሞ ሩቅ ሳንሄድ የጣልያን ዘመን አርበኝነቱ በ ቂ ምስክር ይሆናል።ስለዚህ የአሜሪካኖችን ድጋፍ ያገኘ ሁሉ በፈላጭ ቆራጭነት ይገዛል ማለት ከንቱ ምኞት ነው።

በዚሁ አያይዘን ጠቅላላውን የአለም ሁኔታ የተመለከትን እ ንደሆነ የህዝቦች ሁሉ ጠላት የሆነው ኢምፔሪሊዝም በያለበት እየተወ ጠረ ሲያዝ እናያለን።በእስያ በተለይም በኢንዶቻይና ህዝቦች ፀረኢም

ፔሪያሊስት አንድነታቸውን አጠንክረው ትግላቸውን በመምራት ላይ ና
ቸው።የላቲን አሜሪካ ህዝቦች የያንኪዎችንና የአሻንጉሊቶቻቸውን ብ
ዝበዛ ለመቋቋም በያለበት ለትግል ተሰማርተው ይታያሉ።በአፍሪቃም በ
አንጐላ፤በጊኔ (ቢሳው)፤በሞዛምቢክ፤በደቡብ አፍሪቃና በዚምባብዌ የሀ
ዝቦች የነፃነት ትግል እየተፋፋመ ሄዷል።በመካከለኛው ምስራቅ ከሃያ
አመታት በፊት ቤትና ንብረቱን ለቅቆ የተሰደደው የፍልስጤም ህዝብ
ከፅዮናዊያን፤ከኢምፔሪያሊስት ጠባቂዎቻቸውና ከአረብ አድሃሪዎች ጋ
ራ የሚደርገው ትግል እንደ ሰደድ እሳት ቀበሌውን በማዳረስ ላይ ነው
በያለበት የተበዝባጋር ህዝቦች ትግል እየደረጀ ሄዷል።የዚህ አለም-አ
ቀፍ ትግል አውሎ ንፋስ በኢትዮጵያችንም ላይ መንፈሱ ምንም ጥርጥ
ር የለውም።ኢምፔሪያሊዝም ተደምስሶ ህዝቦች ነፃ እስኪወጡ ድረስ ት
ግሉ እየተፋፋመ የሚሄድ መሆኑ ግልፅ ነው።

ባጭሩ ከዚህ በላይ እንደዘረዘርነው መጭው ጊዜ በየምክን
ያቱ የተጠራቀመ የትግል ማእበል ያዘለ መሆኑን ለማሳየት ሞክረናል።
የዚህ አውሎ ንፋስ ዋና መነሻ አድርገን የምንቆጥረው የጊዜውን የሀገ
ራቱን የኢኮኖሚ፤የሶሻልና የፖለቲካ ሁኔታ ነው።በዝባዦቹ የሚያደር
ጉትም ፀረህዝብ መፍጨርጨር የወሰደውን መልክ ቢወስድ ዞሮ ዞሮ አ
ላማው የህዝባችን መበዝበዝ እንዲቀጥል፤አንድነቱ ጠፍቶ እንዲደክም
ዘልአለማዊ የሚመስላቸው ስርአታቸው እንዳይናጋ መሆኑን እናውቃ
ለን።

ታድያስ ኢትዮጵያን ለማዳን? ነፃነታችንን ለመጐናፀፍ ?
ወደፊት ለመራመድ? እኛ ለዚህ ከአንድ መንገድ ሌላ ምንም አይታየ
ንም።የኢትዮጵያ ተበዝባጋር ህዝብ እውነተኛ ጠላቶቹን ከኢትዮጵያ መ
ሬት ለማጥፋት ባንድነት ተደራጅቶ መታገል አለበት።የኢትዮጵያ ህዝ
ብ ጠላቶቹን ወደጐን እየተወ እርስ በእርሱ እንዲፋጅ አንፈልግም።የ
ኢትዮጵያ ህዝብ ከዘመን ዘመን የላቡን ፍሬ መገበሩ አንሶት ለጥቂት ስ
ግብግቦች ጥቅም ማዳበሪያ ደሙ እንዲፈስ፤ወንድማማች ልጆች በከንቱ
እንዲተላለቁ አንፈልግም።ነገር ግን አውሎ ንፋሱን ገምተን ከአሁኑ ል
ንቋቋመው ካልተደራጀን ነገ በሚደረው ትንንቅ ህዝባችንን በዝባዦች
ሲያወናብዱት፤ከግራና ከቀኝ ኢምፔሪያሊስቶች ግራ ሲያጋቡት ሁሉም



በጠባብ መንደሩ፤በጠባብ ነገዱ፤በጠባብ ሃይማኖቱ ተውተብትቦ የሰፊው
ን የኢትዮጵያ ህዝብ መሰረታዊ አንድነት ዋናውን የድህና የሀብታም
ትንንቅና እውነኛውን የነፃነት ትግል ማሰብ ይቸግራል።ዝለዚህም በመ
ሰረቱ ፀረባላባትና ፀረኢምፔሪያሊስት የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግ
ል ሊዘበራረቅና ለጊዜው የተፈለገውን ውጤት ላያስገኝ ይችላል።

የኢትምጵያ ህዝብ ጭቆናን ለመቋቋም በያለበት በመነሳሳ
ት ላይ ነው።የህዝባችን ትግል በያለበት ከተደራጀ ትግሉ የሚያስከትለ
ውን መከራ ለመቀነስም ሆነ የሚያስገኘውን ፍሬ ዋጋ ያለው ለማድረግ
ይቻላል።ስለዚህም ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ እውነተኛ ሰላም፤አንድነት፤ነ
ፃነትና እርምጃ የሚቆረቆር ሁሉ ፀረባላባትና ፀረኢምፔሪያሊስት አላማ
ላይ ተመስርቶ የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ ባአንድ ግንባር የሚያሰልፍ
የትግል ድርጅት እንዲቋቋም መጣር አለበት።

ለመሰረታዊ ለውጥ እንቅፋት የሆኑትን ፀረህዝብ ሀይሎች
ህዝቡ በሙሉ በአንድነት ተደራጅቶ ሊታገላቸውና ሊደመስሳቸው ይገ
ባል።ለዚህም ዛሬ የገዢው ቡድን በሚያደርገው ምስጢራዊ ዘረፋና የ
ውርስ ዝግጅት አንፃር ህዝቡ በግልፅ ለለውጥና ብዝበዛን ጨርሶ ለማጥ
ፋት የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት።ለዚህም ከሁሉ
አስቀድሞ በህዝቡ መሰረታዊ ፍላጐቶች ላይ የተመሰረተ ግልፅ የስራ
ፕሮግራም ያስፈልጋል።የዚህ ፕሮግራም ዋና ዋና መልኮቹ ከዚህ በፊት
በተማሪዎች ጉባኤዎች ተደጋግመው ተገልፀዋል።

ዋናው አላማ የጪሰኛ ገበሬና የላብ አደሩን ጥቅም ለመጠ
በቅና ለማደራጀት ነው።ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሊወሰን አይገባም።አይች
ልምም።ሌሎችም በባላባቶችና በኢምፔሪያሊስቶች ዘረፋ የተመረሩ አ
ገር ወዳድና የህዝብ ወገኖች ሞልተዋል።ስለዚህ ይህ ፕሮግራም የነዚህ
ንም የህዝብ ወገኖች ጥቅም የሚጠብቅ ሰፊ የስራ ውጥን መሆን አለበት

-ll-

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ከተውተበተበበት አዘቅት ወጥቶ አ
ዲስ ህይወት ይጠይቃል።መብቱም ነው።በሃብታምና በለምለም ሃገር ው
ስጥ ላቡን አንጠፍጥፎ የሚኖር ህዝብ ከድህነት፤ከርሃብና ከድንቁርና ጨ
ርሶ የተፋታና በደንብ የተሟላ ኑሮ ሊኖር ይገባዋል።የሀገራችን ህዝ

ብ በሙሉ ከህፃን እስከ ሽማግሌ ጤናው በደንብ ሊጠበቅ ይገባል።የሃገ
ራችን ወጣቶች በሙሉ የትምህርት ብርሃን ማግኘት አለባቸው።በቂ ጉ
ልበትና ትምህርት ያለው በሙሉ ሰርቶ ራሱን ለመቻል መብት አለው።
ባለውለታው አርበኛ፣ጡረ ያጣው ላብ አደር፣ሰብሳቢ ያጡት ህፃናት ሁ
ሉ ከሚገኙበት የሰቀቀን ኑሮ ተላቀው፣በሃገራቸው ያጡትን እምነት፣በ
ሰውነታቸው ያጡትን ኩራት መልሰው መጐናፀፍ አለባቸው።ህዝቡ በ
ሙሉ ንፁህ ውሀ ያስፈልገዋል።የመብራት ሀይል ያስፈልገዋል።ቁሳቁሳ
ዊ (material) ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ፍላጐቱን የሚያረካባቸው የመ
ያላቻ ድርጅቶች ያስፈልጉታል።ለዚህም በቂና የተወሰነ የእረፍት ጊዜ
ያስፈልገዋል።ይህ ነው የተሟላ ኑሮ።ይህ ነው የሚጨበጥ ነፃነት።

የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህን መሰረታዊ ፍላጐቱን ለማርካት
ተደራጅቶ መታገል አለበት፤ይታገላልም።የበዝባዦቹ የፕሮፓጋንዳ ጋጋ
ታ እስከአጥንቱ ሰርስሮ የገባውን ድህነት፣መራቆትና ቅጥ ያጣ የኑሮ ፈ
ተና ሊያስረሳው አይችልም።እነዚህንም ፍላጐቶች ለማርካት ፈጣንና ት
ልቅ የኢኮኖሚ እድገት ያስፈልጋል።በያለበት ፋብሪካ ማቆም፣ግድብ መ
ገንባት፣መስና መቅደድ፣በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም፣የእርሻን ዘዴ ማ
ሻሻል፣በጭሩ የሃገራችን ይህ ነው የማይባሉና የተሰበጣጠሩ የተፈጥሮ
ና ሰብአዊ ሃብቶች ለመላው ህዝብ ጥቅም ስራ ላይ መዋል አለባቸው።

እነዚህ ፍላጐቶች ሰፊና ጥልቅ በመሆናቸው በቀላሉ ሊከና
ወኑ አይችሉም።የመላ ህዝቡ ፍላጐቶች ስለሆኑ በጠቅላላው የህዝቡን
የተደራጀና ሆን ብሎ የተነሳ ጥረት ይጠይቃሉ።ሃገራችን ሀብታም ነች።
ህዝባችን ታታሪ ነው።ኑሮው ባይሙዋላ ህዝቡ በሙሉ ታጥቆ የሚባክ
ነው ለጥቂት በዝባዦች መትረፍረፍ በመሆኑ ነው።ስለዚህም ይህ ጥቂ
ቶች በጥቅም ተሳስረው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጫኑት የብዝበዛ ስርአ
ት ተሰባብሮ መውደቅ አለበት።በሱም መቃብር ላይ እነዚህን የህዝብ ፍ
ላጐቶች ለማርካት ህዝቡ ተደራጅቶ የሚሰራበትና ጥቅሙን የሚያዳብ
ርበት፤ወደፊትም የሚራመድበት አዲስ ህዝባዊ ስርአት ያስፈልጋል።

ከሞንታርጋ ጉባኤያችን ወዲህ ለዚህ ሁሉ በኢትዮጵያ
"ህዝባዊ መንግስት" አስፈላጊ መሆኑን አስረድተናል።ለዚህም ህዝባዊ
መንግስት የተደራጀ ህዝባዊ ትግል ያስፈልጋል።የሚደራጀው ማነው?



ይህን ለመረዳት ትግሉ ከማን ጋር እንደሆነና የትግሉስ ውጤት ማንን
እንደሚጠቅም መመልከት ያስፈልጋል።

የዛሬው የንጉሰ ነገስት መንግስት የንጉሰ ነገስቱን፤የታላላቅ
ባላባቶችን፤የታላላቅ ከህናትን፤የከፍተኛ ሹማምንትን፤የባእድ በዝባዦ
ችን ጥቅም ለመጠበቅ የቆመ፤የዘራፊዎች "ወኪል ድርጅት" ነው።እኛ ደ
ግሞ የህዝብ መንግስት የምንለው ዛሬ ተደራጅተው የሚጨቁኑትን ዘ
ራፊዎች በሙሉ አስወግዶ የህዝብን ጥቅም የሚጠብቅ "ወኪል ድርጅ
ት" ይሆናል ማለት ነው።የህዝብ መንግስት ሲባል የዛሬን በዝባዦች በ
ሀይል ሰብሮና ከስልጣን አስወግዶ በሱ ቦታ የዛሬ ተጠቂዎች በሙሉ በ
አንድነት ተደራጅተው ጥቅማቸውን የሚጠብቁበት አዲስ ስርአት ይዘ
ረጋል ማለት ነው።እዚህ ላይ የዛሬን በዝባዦች ነጥለን ያሳየነውን ያህል
በዚህ ስርአት ውስጥ የተጨቆኑት ክፍሎች እነማን እንደሆኑ ማሳየት
ያስፈልጋል።እርግጥ ዋና ተጠቂዎች በትግሉ እስከመጨረሻ የሚገፉት
ጢሰኛ ገበሬዎችና ላብ አደሩ መሆናቸው ጥርጥር የለውም።ግን ዛሬ በ
ኢትዮጵያችን ለውጥንና እርምጃን የሚፈልጉ፤በባላባቶችና በባእድ ባ
ለገንዘቦች የተጨቆኑ፤ስለዚህም ለመታገል የሚችሉና የሚደራጁ ሌሎ
ችም አሉ።ለሃገሪቱ እርምጃና ለህዝቡ ደህንነት ለመታገል እነዚህም ፀ
ረባላባትና ፀረኢምፔሪያሊስት አገር ወዳድ ሀይሎች በትግሉም ውስጥ
ሆነ በነገይቱ ህዝባዊት ኢትዮጵያ ተገቢ ቦታቸውን ማግኘት አለባቸ
ው።ስለዚህ ህዝብ ስንል ጢሰኛ ገበሬንና ላብ አደሩን ብቻ ሳይሆን በአ
ሁኑ ጊዜ በየባላገሩ ከጢሰኛው ገበሬ በማይሻል የኑሮ ደረጃ እየማቀቀ
የሚኖረውን ባለመሬት አርሶ በላና በታላላቆቹ ባላባቶችና በባእድ በዝ
ባዦች ታፍኖ የቀረቀዘውን የሃገርየውን ነጋዴ፣ችጋር ከባላገር አባሮት
ስራፈትነት ያንገላታቸውን የከተማ ችግረኛ፤በያለበት ተሰማርቶ የእው
ቀትን ብርሃን ለማስፋፋት በኑሮ ጠርዝ ላይ የሚባክነውን አስተማሪ፤በስ
ርአቱ ታፍኖ ለሃገሩ እንዳይሰራ የተከለከለውን ምሁር፤ለህዝብ የሚረዳ
እውቀት እንደውሃ የጠማውን አገር ወዳድ ወጣት . . . ወዘተ፣በጭሩ ከ
ላይ የጠቀስናቸው በዝባዦችና አጫፋሪዎቻቸው በስተቀር በመላ የኢ
ትዮጵያን ህዝብ እየጨመርን ነው።

ህዝባዊው መንግስት ከላይ የዘረዘርናቸውን ልዩ ልዩ የህዝ

ብ ክፍሎች ተገቢ ጥቅም በደንብ ይጠብቃል።ለዚህም ከላይ የጠቀስና
ቸውን መሰረታዊ የህዝብ ፍላጐቶች ለማርካት ግልፅና አጠቃላይ የሆ
ነ የስራ ፕሮግራም በትግሉ ውስጥ መተለም አለበት።

የዚህ ፕሮግራም ዋና ዋና መልከቹ ከዚህ በፊት በተግሪ ስ
ብሰባዎች ላይ ተወስተዋል።ዋናው አላማ መቸም የጊዜውን የበዝባገ
ች መንግስት አስወግዶ በሱ መቃብር ላይ ከባላባት ጭቆናና ከኢምፔሪ
ያሊዝም ብዝበዛ የተላቀቀ ህዝባዊ መንግስት ለማቋቋም መጣር ነው።
ይህ ህዝባዊ መንግስት በዛሬው አገዛዝ ስር ተረግጠው የተያዙትን የህ
ዝቡን ሰብአዊ መብቶች ያከብራል፤የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚ
ደረገውን ጥረት ያቅዳል፤ይመራል፤ያቀናብራል፤እውቀትን ያስፋፋል፤ሰላ
ምን፤አንድነትንና እኩልነትን፤በሃገሪቱ ያሰፍናል፤በነገዶችና በሃይማኖቶ
ች መካከል ያለውን ግጭት በትክክልና በእኩልነት ይፈታል፤በፆታ መ
ካከል ያለውን ልዩነት ይሰርዛል፤በጠቅላላው ለህዝብ ነፃነት፤እኩልነት፤አ
ንድነት፤ሰላምና ብልፅግና ይጥራል።

ለሀገራችን እርምጃ ለህዝባችን ደህንነት የሚታየን አንድ
መንገድ ይኸው በግልፅ የስራ ውጥን ላይ የተደራጀ የህዝብ ትግል ብ
ቻ ነው።ህዝባችን ለሚያጋጥመው ችግር መፍትሄ የሚገኘው ነገድ በነ
ገድ፤ሃይማኖት በሃይማኖት ላይ በመነሳቱ አይደለም።ተበዝባጋር በተበዝ
ባጋር ላይ ቢነሳ ይበልጥ መከፋፈልንና ይበልጥ ጭቆናን እንጂ ነፃነትን አ
ያተርፍም።ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ በዝባገሮች ከሚነዙት የጥ
ላቻና የመከፋፈል ፕሮፓጋንዳ ተጠብቆ አንድነቱን እንዲያጠነክር፤ህዝ
ባችን ትርፍ ከሌለው የእርስ በርስ እልቂት ተጠብቆ ቁጣውን፤ሀይሉን
ና ጉልበቱን ለመሰረታዊ ለውጥና ለነፃነቱ ትግል እንዲያውለው ያስፈ
ልጋል።

ህዝቡን በአንድ የትግል ግንባር ማደራጀት ፍፁም ቀላል ተ
ግባር አይደለም።ይህ እርምጃ ብዙ ድካምና ብዙ መስዋእትነት ይጠይ
ቃል።ነገር ግን ዝም ብሎ መቀመጥ ደግሞ ይበልጥ አሰቃቂ ነው።ህዝባ
ችን በድህነት፤በድንቁርና፤በበሽታና በመከራ እየተፈተነ ወግ የለሽ ኑሮ
ውን ይቀጥላል።በዚህም ቁጣ የእውር ድንብሩን ተራ በተራ እየተነሳ ሲ
ፍጨረጨር ተራ በተራ ይደመሰሳል።ከዚህ አዘቅት ያለቆራጥ ትግል መ



ውጣት ከንቱ ህልም ነው።ያልተደራጀ ትግል ደግሞ ሺህ ጊዜ ቆራጥ ቢ
ሆን የድብላ ጉዞ ነው ና መደናበርን መትራመስንና መደምሰስን እንጂ
ድልን አያስገኝም።

የመላ ኢትዮጵያ ህዝብ የእውነተኛ ሰላም፤ነፃነትና አንድነ
ት የተያዘው በዚህ በአንድነት በምንመሰርተው የትግል ግንባር ብቻ ነ
ው።ሌላ ምንም መንገድ የለም።

(1) Ethiopia: an empire feeling its age. Richard West Supplement "Sunday Times" June 1964
(2) Ethiopia: A New Political History. R. Greenfield pp. 89
(3) Journal of Ethiopian Studies Vol. II No. 2 A preliminary history of the tripartite Treaty of December 13, 1906, by Harold G. Marcus.
(4) "Le Monde" 8-9 Fevrier 1970

# ግልፅ ደብዳቤ ለአጉል ገለልተኞች

ዛሬ በሃገራችን የለውጥ አውሎ ነፋስ ማንዣበቡ አይኑን ከፍቶ ለማየት የሚሻ ሁሉ ግልፅ ነው።የሚገርመው ታድያ፣በያለበት የኢትዮጵያ ህዝብ የጭቆናን ሃይሎች ባለው ሃይል እየተቋቋመ ወጣቱ፣ሽማግሌው፣ወንዱና ሴቱ በሚዕቃይበት፣ቤቱና ንብረቱ በሚፈታበት ወቅት "እኔ ገለልተኛ ነኝ" ለማለት የሚቃጣው አወናባጅ መብዛቱ ነው።ሁሉ "ገለልተኛ" ነው።ጉዳዩ አይመለከተውም።ይህ ታድያ እውነት ነው ወይ? ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ትግል እየተፋፋመ በሚሄድበት ወቅት በጨቋኝና በተጨቋኝ መካከል ሆኖ አስታራቂ፣ከዳር ሆኖ ታዛቢ መሆን ይቻላል ወይ? በፍፁም አይቻልም።በተያዘው ትግል ማንም ኢትዮጵያዊ ገለልተኛ ሊሆን አይችለም።ከሁሉ ይበልጥ የማንቀበለው ደግሞ አንድ አንድ የትግሩ "ገለልተኞች" ነን ሊሉን ሲሞክሩ ነው።ስንት ጊዜ እንለፍልፍ? በታሪክ ሃይል ከተወረወርንበት ለዘራፊ አዳሪነት፣አውቀንና ፈቅደን በግልፅ ወደ ህዝቡ እስክንሸጋገር ድረስ እኛም ዘራፊዎች ነን።ገለልተኞች አይደለንም።

ዛሬ በኢትዮጵያችን በየአውራጃው፣በየመንደሩ፣በየቀበሌው የሚፈፀመው ግፍ፣የሚበዘበዘው የህዝብ ሀብት፣የሚፈሰው የህዝብ እንባ ከመቸውም ይበልጥ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ይመለከተዋል።የአስተዳዳሪው (የቢሮክራቱ) ደመወዝ፣"የተቀምጦ-በላው" ሃብታም መንሸራሸሪያና መንደላቀቂያ፣... ወዘተ እያንዳንዱ ገበሬና ላብ አደር እየተወጠረ ከሆዱ ነፍጎ፣ከሚስቱ ነፍጎ፣ከልጁ ነፍጎ የሚያስረክበው የላብ ፍሬ ነው።በተጨቋኙ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ፣በየቀኑ ለሚወርደው መከራ ሁላችንም እየጨመረ የሚሄድ ሃላፊነት አለብን።"የተማሩ ወጣቶች" የዚህ ብዝበዛ ተጠቃሚዎች በመሆናቸው ራሳቸውን እንደታዛቢ ቆጥረው ሌሎችን ማግረር ብቻ ከዚህ ሀላፊነት አያስጥላቸውም።ሳንወደውና ሳንፈቅደው ከተወረወርንበት የጨቋኞቹ ወገን አውቀንና ፈቅደን እስክንወጣና ከህዝብ እስክንደባለቅ ድረስ፣በየመንደሩ ከሚጉሳቆለው፣ከሚጉላላውና ከሚዋረደው ሃገረ ሰብእ ጋር መጉሳቆላችን፣መጉላላታችንና መዋረዳችን እስካልተሰማን ድረስ እኛም ጨቋኞች ነን።ገለልተኞች አይደ



ለንም።

በጭቆና ላይ ጭቆና፣በብዝበዛ ላይ ብዝበዛ እየተጨመረበት የሚሄደው የኢትዮጵያ ህዝብ ትእግስቱ አልቆበታል።ከእንግዲህ የነፃነቱንና የክብሩ፣ዋስትና መሳሪያውን አፈፍ አድርጎ ጨብጦ ጨቋኞቹን መቋቋም ብቻ መሆኑ ገብቶታል።በሚመጣው የሪቮሉሽናዊ ትንንቅ ለታዛቢና ለገለልተኛ ምንም ቦታ የላቸውም።የነፃነት ትግል የኳስ ጨዋታ አይደለም።ዳኛና ተመልካች የለውም።በህብረተሰቡ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ግለሰብ ከዚህ ወይም ከዚያ አንዱን ወገን የግድ መርጦ በሙሉ ሀይሉና በሙሉ ልቡ መሳተፍ ይኖርበታል።

ታዛቢ ሊኖር አይችልም የምንለው የዚህን ትንንቅ መነሾ፣የአውሎ ንፋሱን ሀይለኝነትና የሚጠበቀውንም ውጤት በመመልከት ነው።የነፃነት ትግል ረጅም፣አታካችና መራር ትግል ነው።ስርአተ ማህበራችን ድብልቅልቁ ወጥቶና ትንንቁ ተፈፅሞ የህዝባችን የነፃነት ትግል ከታሰበው ግብ ሲደርስ ማንም ሰው እንደቀድሞው አይሆንም፣ብዙ መሰረታዊ ለውጦች ይኖራሉ።አውሎ ንፋሱ ባለፈበት ሁሉ በግለሰቡ፣በቤተሰቡና በህብረተሰቡ፣በጠቅላላው በሃገሪቱ፣የቀድሞው የገዢና የተገዢ መንፈስ በሙሉ ተጠራርጎ ተጥሎ፣የአዲስ ኢትዮጵያና የአዲስ ኢትዮጵያዊ ፅኑ መሰረት በያለበት ስር ሰዶ እናገኘዋለን።መራራው ትግል አልፎ ፀሀይቱ ስትወጣ የቀድሞዋ ፀሀይ አይደለችም።ያኔ ለሁሉም ታበራለች።የቀድሞ ኢትዮጵያዊያን ገዥም ሆኑ ተገዥ በአንድነት ድምጥማጣቸው ጠፍቷል።ከእንግዲህ አዲስ ሰው፣አዲስ ኢትዮጵያዊ ነው።

በአንድ ወገን በትግሉ ጊዜ ለነፃነቱና ለክብሩ ህይወቱን ለመሰዋት ቆርጦ የተናነቀ፣ደጋግሞ ከሞት አፋፍ እየደረሰ የተመለሰ፣የነፃነቱንና የክብሩን ዋጋ በእናቱ፣በአባቱ፣በእህቱ፣በወንድሙ፣በሚስቱ፣በልጁና በወዳጁ መከራ የከፈለ፣በባርነት ሞቶ በነፃነት የተነሳ፣ሊከፍል በተሰናዳው በህይወቱ ዋጋ ባርነቱን አሽቀንጥሮ ጥሎ ነፃነትን የገዛ፣ጭቆናን የማይወድ፣በትግልና በፈተና ወደሰብአዊነት የተነሳ፣አዲስና ኩሩ ሰው እናገኛለን።በሌላው በኩል ደግሞ ያለው እንደዚሁ በዚሁ በትንንቅ ጊዜ ለጨቋኝነቱ ዋጋ የሱ በሆኑት ሁሉ የከፈለ፣ራሱም በመከራ የተፈተነና ከቀድሞው የገዥነትና የበላይነት ልክፍት፣ስሜትና ቅዠት የአገሬው አፈ

ሙገዝ አላቅቆት፣የሰው ልጅን እኩልነት በግዱ አምኖ የተቀበለ፣እሱም ወ
ደሰብአዊነት የተመለሰ አዲስ ሰው ይሆናል።

ባጭሩ ረጅም ትግላችን ሲፈፀም ይህ አውሎ ንፋስ በአስተ
ሳሰባችው ያልለወጣቸው፣በጥቅማቸው ያልነካቸውኛጨቋኞች እንደነበሩ
እንደቀድሞ የሚጨቁኑ፣ተጨቋኞች እንደነበሩ እንደቀድሞው የሚጨ
ቆኑ ሊኖሩ አይችሉም።ከዚህ ቀጥሎ፣ከዚህ ትንንቅ፣ከዚህ እሳት፣ከዚህ ድ
ብልቅልቅ ውስጥ ገብቶ ሳይፈተን ጸሚወጣ ፍጡር አይገኝም።ታድያ እ
ዚህ ውስጥ ከመሀል ሆኖ አስታራቂነት፣ከዳር ሆኖ ገለልተኝነት ይቻል ይ
መስላችኋል? እኛ አይመስለንም! ስለዚህ ዛሬ "ባትመርጡ" ነገ መሀል
መቆም ሲቸግር የግድ በታችሁን እንድታስታውቁ ትገደዳላችሁ።

እዚህ ላይ በተለይ ለውጥንም ሆነ ባሉበት መቆምን በመፍ
ራት በበዝባዦቹና በህዝቡ መከከል "ሶስተኛ መንገድ" ያገኛችሁ እየመ
ሰላችሁ" ጥገናን" የሙጥኝ ያላችሁትን ምሁሮች የያዛችሁት መንገድ ም
ንም አይነት ዘለቄታ እንድሌለው ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።ዛሬ በኢ
ትዮጵያ የሚያስፈልገው ለውጥ የእያንዳንዱን ገበሬና የእያንዳንዱን ሰ
ራተኛ በጠቅላላ የህዝቡን ኑሮ በይበልጥ የተሙዋላ የሚያደርግ ለውጥ
ነው።ለዚህም ህዝብ ጠላቶቹን ደምስሶ እድሉን እጁ ማስገባት አለበት።
እናንተ ህልማችሁ የበዝባዦችን ጥቅም ሳትተናከሉ፣ከዚህም የሚወረ
ወርላችሁ ጉርሻ ሳይቆነጠርለት የህዝቡ ደህንነት ሳይሆን የህዝብ "ፀጥ
ታ" የሚጠበቅበትን ዘዴ ለማግኘት ነው።ምንም መሰረታዊ ለውጥ ሳይ
ደረግ "የሁሉ ኢትዮጵያዊያን" ጥቅም የሚጠበቅበትን ዘዴ ለማግኘት
ትወድቃላችሁ፣ትነሳላችሁ፣ትተቻላችሁ፣ትፈለስፋላችሁ።በሀብታምና በ
ድሀ፣በጨቋኝና በተጨቋኝ የተከፈለ ህብረተሰብ ውስጥ "የሁሉንም ጥቅ
ም" በአንድ ላይ እንዴት መጠበቅ ይቻል ይመስላችኋል? በሀገራችን
ድሀ፣አልቃሽ፣ተበዝባጋርና ተዋራጅ መኖሩ ግፈኛ፣በዝባጋርና አዋራጅ በ
መኖሩ መሆኑን "የተማራችሁት ገለልተኞች" እንዴት አጣችሁት? በአ
ንድ ሀገር፣በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ይቆራኙ እንጂ ድሃና ሃብታም እ
ኮ የሚኖሩት ሁለት አለም ውስጥ ነው! የህዝብ ነፃነት አለ፤የበዝባዦች
ነፃነት አለ፤የህዝብ እውነት አለ፤የበዝባዦች እውነት አለ።የህዝብ ፍት
ህ አለ፤የበዝባዦች ፍትህ አለ።የህዝብ ደህንነት አለ፤



የበዝባዦች ደህንነት አለ።የበዝባዦች ሙብት ህዝብን መጨቆ
ን ነው።የህዝብ ሙብት ደግሞ የነሱን ጭቆና ተናንቆ መጣል ነው።ነፃነ
ታቸው ከሁሉ አስቀድሞ እንደልብ የመዝረፍ ነፃነት ነው፤የህዝቡ ነፃነ
ት ደግሞ ከሁሉ በፊት ዘረፋን መቋቋም ነው።የበዝባዦች ሀብት መሰረ
ቱ የህዝቡን ላብ መግፈፍ ነው።የህዝብ ሀብት መሰረቱ ሁሉም የላቡን
ፍሬ አለመገፈፉ ነው።ባጭሩ ለህዝቡና ለበዝባዦቹ አንድ ትርጉም የ
ሚሰጠው ምንም ቃል የለም።ስለዚህም በበዝባዦች ስርአት ውስጥ በ
አንድነት "የሁሉም" ጥቅም የሚጠበቅበት ምንም አይነት ተአምር ሊኖ
ር አይችልም።ዛሬ የነሱ ነፃነት የህዝብ ባርነት ነው፤ነገ የህዝብ ነፃነት የ
ነሱ መደምሰስ ይሆናል።

ስለዚህ ሺህ አመት ብትመራመሩ፣ሺህ ከማስዮን ቢፈጠርላ
ችሁ፣ሺህ ሚኒስቴር ቢቋቋም፣የበዝባዦቹ ጥቅም ከመሰረቱ ሳይነካ የኢ
ትዮጵያን ህዝብ ጥቅም ማዳበር አይቻልም።

እንደዚህ "እጥንታችሁ" ከላይ ለህዝቡ የምትወረውሩለት
በወረቀት ላይ የሚውል "የመሻሻል" ፕላን ህዝቡ የሚያስፈልገውን ጠ
ቅላላ ለውጥ ሊያስገኝለት አይችልም።ዛሬ በሀገራችን የጥገና ለውጥን
ጠልተን መሰረታዊ ለውጥን የምንሻው የነገው ኢትዮጵያዊ በአካሉ የ
ፋፋ፣በአስተሳሰቡና በመንፈሱ የዳበረ፣በእውቀቱ የላቀ፣ከተውተበተበበት
የሰው ልጅ መንፈሳዊ ኩራት ጠንቆች ፈፅሞ የተላቀቀ ሙሉ ሰው እን
ዲሆን ስለምንመኝ ነው።"መሬት ላራሹ" ስንል አላማችንና ትግላችን አ
ራሹ በያለበት የላቡን ፍሬ ሳይቀማ ለራሱ ለቤተሰቡና ለህብረተሰቡ ደህ
ንነትና እርምጃ ያውለው የሚል የእንጀራ ትግል ብቻ አይደለም፤"መሬ
ት ላራሹ" ስንል ህዝባችን ከላቡ ፍሬ ጋር፣ከመሬቱ ጋር፣አብሮ የተቀማው
ን በራሱ ያለውን እምነት፣በስርቆ አዳሪነቱ ያለውን ኩራት እንደገና ተጉ
ናፅፎ የተገፈፈውን ሰብአዊነቱን መልሶ እንዲያገኝ ነው።"መሬት ላራሹ"
ስንል ባላባቱ ደግሞ እንደዚሁ ከሚዘርፈው ሀብት ጋር የሚያግበሰብሰ
ውን የሰርቶ አዳሪነት ጥላቻና ንቀት ተላቆ እሱም ወደሰብአዊነት የተመ
ለሰ ፍጡር እንዲሆን ነው።ለዚህም የነፃነት ትግላችን ሙሉ ውጤቱን አ
ስገኝቶ ህዝባችን ከማንኛውም ልክፍት ስሜቶችና የሰው ልጅ መንፈሳ
ዊ ኩራት ጠንቆች የሚላቀቀው ከናንተ እንደሰማይ መና በሚወርድለት

የጥገናዊ ለውጥ ችሮታ ሳይሆን ራሱ በትግሉ ተደራጅቶ ይገባኛል ብሎ ሲወስድና ይህም ትግል ለሚያስከትለው መስዋእትነት ዝግጁና ብቁ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው።

ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያስፈልገው መሰረታዊ ለውጥ በዚህ ወይም በዚያ ፀሀፊ ጥረት የሚገኝ ነገር አይደለም።ይህ መሰረታዊ ለውጥ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ፣ህዝቡን በሙሉ፣የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ተደራጅቶና ተጋግዞ በሚያደርገው ጥረት የሚገኝ ጠቅላላ ለውጥ ነው።እንደዚህ ያለው የህዝብ ጥረት ፍሬ እንዲሰጥ ከተፈለገ አስቀድመው የህዝብ ጠላቶች ከህገራችን ገፅ መጥፋት አለባቸው።ይህ ጥረት ለጊዜው ከሁሉ ተቀዳሚነት የሚሰጠው የነፃነት ተጋድሎ ነው።የህዝቡን ወገን የመረጡ በምንም ፀረህዝብ ፕሮፓጋንዳ ሳይወናበዱና ሳይጭበረበሩ፣ይህን ትግል ይበልጥ ለማፋፋምና ለማደርጀት የማይቆጠብ ጥረት ያደርጋሉ።የህዝቡን ጠላቶች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የመረጡ ደግሞ ይህን የነፃነት ተጋድሎ በየምክንያቱ እያንቋሸሹ አጉል ተስፋ በመሰንዘርና የማያዋጣ የጥገናዊ ለውጥ ጉዳና በማሳየት የህዝቡን ትግል ለመግታት፣ለማድከምና ለማጭበርበር ይጥራሉ።በነዚህ በሁለት ተቃራኒ መንገዶች መሃከል ሶስተኛ መንገድ ሊኖር አይችልም።

ይልቁንስ ተነሱ! ዛሬ እያንዳንዱ የተማረ ወጣት ታላቅ የትውልድ አደራ አለበት።ይህ የትውልድ አደራ ገለልተኛ ነኝ እያሉ እንደሰጐን አይን መጨፈን አይደለም።ከዘራፊዎች ተደባልቆ መዝረፍ አይደለም።ከተበዝባዦች ተደባልቆ ለመራራ ልቅሷቸው ሙሾ ማውረድ አይደለም።የትውልዳችን ዋና አደራ ህዝባችን በረጅም የነፃነት ትግል ታሪኩ ደጋግሞ ባፈራቸው ተጋዳዮች አርአያነት በመመራት የኢትዮጵያችንን የእውነተኛ ነፃነት ቀን ለማብሰር ከሚታገሉ ሀይሎች ጋር ተደባልቆ ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር መሰለፍ ነው።



## የኢምፔሪያሊስት ብዝበዛ

ከአንድ መቶ አመታት በፊት በምእራብ አገሮች የፋብሪካ ስራ በጣም ተስፋፍቶና ይበልጥም ለማደግ አገር ጠቦት ይገኝ ነበር።በሰፊውና በብዛት የሚሰሩት የፋብሪካ እቃዎች ከሚሰሩበት አገር እየወጡ እንዲሸጡ ገበያ አስፈለገ።ለፋብሪካዎች ማካሄጃ በሃገር ውስጥ የሚገኘው ጥሬ እቃ አልበቃ ስላለ በያለበት የጥሬ እቃ ምንጭ መፈለጉ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ሆነ።ስለዚህም ቀደም ብለው የተያዙትና በመያዝም ላይ የሚገኙት የአፍሪቃ፣የእስያና የላቲን አሜሪካ ለዚህ ጥንድ ችግር መልከም መፍትሄ ሆኑ።እነዚህ አገሮች መጀመሪያ የሸቀጥ ማራገፊያ ከዚያም የጥሬ እቃ ምንጭ ሆነው እራሳቸው እየተበዘበዙና እየተራቆቱ ታፍኖ ለነበረው ለምእራብ አገሮች እድገት የህይወት እስትንፋስ ሰጡት። ተበዝባዥ አገሮች ይህን ሙያ የግድ ከተቀበሉበት ጊዜ አንስቶ የራሳቸው እድገት ተገታ።ከምእራባዊያን ፋብሪካ የሚጐርፈው ሸቀጥ ታዳጊውን የሃገሬውን የእጅ ጥበብ አቀረቀዘው።በዚህም የተበዝባዥ አገሮች እድገት ታፈነ።ተቀጨ።በጠቅላላው የተበዝባዥ አገሮች ኤኮኖሚ ፊቱን ወደምእራብ አገሮች በማዞሩ ስራው ሁሉ ለአገር እድገት ሳይሆን ለምእራባዊያን ገበያ ታጥቆ መባከን ሆነ።እርሻም ሆነ ኢንዱስትሪ የሚያድገው ለአገሪቱ እድገት በሚስማማው አቅጣጫና ልክ ሳይሆን ለባእድ ኢኮኖሚ ድርጅት እስከአስፈለገ ድረስ ብቻ ሆነ።በእርሻ በኩል ጥረቱ ለህዝቡ ኑሮ የሚያስፈልገውን ሰብል ለማምረት ሳይሆን እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ በምእራባዊያን ገበያ የሚፈሰውን ጥሬ እቃ ለማቅረብ ሆነ። ገበሬዎች እየተራቡ የላባቸውን ፍሬ ለውጭ ገበያ እንዲያስረክቡ ተገደዱ።በቋፍ ለሚኖረው ህዝብ ምግብ የሚሆኑት ሰብሎች እየናቁ በታቸውን ለምእራባዊያን ፋብሪካ ጥሬ እቃዎች ስለለቀቁ ህዝቡ በርሃብና በበሽታ ከመቸውም ይበልጥ ተጠቃ።ለተበዝባዥ አገሮች ኢንዱስትሪ መሰረት ሊሆኑ የሚገባቸው የማእድን ውጤቶችና ልዩ ልዩ ሀብቶች እየተጋዙ የምእራባዊያን ፋብሪካ ማካሄጃ ሆኑ።

በምእራብ አገሮች እንዲህ እየተከማቸ የሄደው ሀብት ቀስ በቀስ በጥቂት መኖፖሎች እጅ እየገባ ሄደ።ልዩ ልዩ የሀብት ምንጮች

ቀስ በቀስ በጥቂት ሰዎች እጅ በመግባታቸው ካፒታሊዝም የተባለው ስርአት መልኩን ለውጦ ከፍተኛ ደረጃው በመድረሱ ኢምፔሪያሊዝም ተባለ ። ይህ ከፍተኛ ደረጃ ወይም ሞኖፖልነት የደረሰው ካፒታሊዝም (ኢምፔሪያሊዝም) ተበዝባጋዥ አገሮችን የሚፈልገው እንደቀድሞው ለገበያውና ለጥሬ እቃ ምንጭነት ብቻ አይደለም።በሀገሩ ውስጥ "ትርፍ" የሆነውን ሃብት እያወጣ ጉልበት ርካሽ በሆነበት፣በተበዝባጋዥ አገሮች በማሰራት ለሚያከማቸው ልክ የለሽ ትርፍ ያስፈልጉታል።ይህንንም ትርፍ የለሽ ሀብት "ዋስትና" ለመስጠት ኢምፔሪያሊስት አገሮች አለምን አንተ በዚህ እኔ በዚያ ተባብለው ይከፋፈሉታል።እነዚህ ሁለቱም ተጨማሪ ጠባዮች የኢምፔሪያሊዝም አይነተኛ ፈሊጦች ናቸው።በያዝነው መቶኛ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ኢምፔሪያሊስቶች አለምን በቅኝ ግዛት፣በእጅ አዙር ቅኝ ግዛትና በሌላም በልዩ ልዩ መልክ ረግጠው ይዘው በያለበት በፈላጭ ቆራጭነት የአለምን ህዝብ ይበዘብዙ ነበር።

ነገር ግን የነዚህ ኢምፔሪያሊስት አገሮች እድገት የተስተካከለ አልነበረም።አንድአንዶች በፍጥነት ሲራመዱ ሌሎች ያዘግሙ ነበር።ስለዚህም የአለም ክፍያ ተደርጐ ባለቀበት ወቅት በደካማነታቸው የተነሳ ትንሽ ወይም ምንም ቅኝ ግዛት ያልደረሳቸው አገሮች ነበሩ።በጊዜው ባላቸውም ሀይል በመጠቀም ከመጠን በላይ የቅኝ ግዛት ያግበሰበሱ አገሮች ነበሩ።ጥቂት ቆይተው ግን ወደኋላ ቀርተው የነበሩ አገሮች (ለምሳሌ ጀርመን) በፍጥነት በማደጋቸው የቀድሞዎቹን ሃይለኞች (ለምሳሌ እንግሊዝን) መስተካከል እንዲያውም መቅደም አመጡ።

እንደአውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1914* አ.ም. እንግሊዝ የያዘችው ቅኝ ግዛት ጀርመን ከያዘችው 12 ጊዜ እጥፍ ሲሆን አሜሪካ ከያዘችው ደግሞ 112 ጊዜ እጥፍ መሆኑ የታወቀ ነው።ነገር ግን በዚህ ወቅት የቀድሞ ደካሞች ጀርመንና አሜሪካ በጣም በልፅገው ለኢንዱስትሪያቸው ይበልጥ ገበያ፣ይበልጥ የጥሬ እቃ ምንጭና ለገንዘባቸው ይበልጥ የትርፍ ማፍሪያ አገር ያስፈልጋቸው ነበር።ግን አዲስ ቅኝ ግዛት ከየት ይምጣ? የቀደሙት "አገር አቅኚዎች" በሙሉ ይዘውታል።ስለዚህ ያለውን እንደገና መከፋፈል የግድ አስፈለገ።የትናንት ደካሞች የሚገባን ይድረሰን አሉ።ክፍያውንም ለማስተካከል በኢምፔሪያሊስቶች



መካከል ጦርነት ተጀመረ። በዚሁ የዘረፋ ድልድል ጉዳይ በያዝነው ክፍለ ዘመን ሁለት የኢምፔሪያሊስት ጦርነቶች ተደርገው በአለም ህዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል መከራ አድርሰዋል።

ከነዚህ ጦርነቶች አንዳንዶች ሀይላቸው ተሰብረው ወጡ፤(ለምሳሌ እንግሊዝ)።አንዳንዶች ደግሞ ከቀድሞ ዳብረው ወጡ፤(ለምሳሌ አሜሪካ)።በጠቅላላው ግን ኢምፔሪያሊስቶች ቀድሞ በአለም ህዝብላይ የነበራቸው ፈላጭ ቆራጭነት ተዳከመ።ከታላቁ የሶቪየት ህብረት ሪቮሉሽን በኋላ ከኢምፔሪያሊስቶች መንጋጋ የተላቀቁት የምስራቅ አውሮፓ፣የቻይና፣የኮሪያ፣የሰሜን ቪትናምና የኩባ ህዝቦች የነፃ ህዝቦችን ሃይል አዳበሩት።ሾሻሊዝምም ከአለም ህዝብ ሲሶው የሚተዳደርበት ስርአት ሆነ። ይህም ማለት ዘራፊዎቹ ኢምፔሪያሊስቶች ብዙ ገበያ፣ብዙ የጥሬ እቃ ምንጭ፣ብዙ ገንዘባቸውን የሚያተርፉበት አገር ተቀነሰባቸው ማለት ነው

የቀሩትም የአለም ህዝቦች ባደረጉት ታላቅ የነፃነት ተጋድሎ የተነሳ ኢምፔሪያሊስቶች ለብዙ የቀድሞ የቅኝ ግዛቶች ቢያንስ ቢያንስ የይስሙላ ነፃነት እንዲሰጡና የብዝበዛቸውን ዘዴና መልክ እንዲለውጡ ተገደዱ።ነገር ግን ዘዴና መልኩ ተለወጠ እንጂ ኢምፔሪያሊዝም በነዚህ አገሮች ላይ እንደቀድሞው የመዝረፍ፣የማፈንና የመራቆት ተግባሩን በፍፁም አላቋረጠም።ሊያቋርጥም አይችልም።ምክኒያቱም እንደዚህ አይነቱ ዘረፋ ለኢምፔሪያሊዝም የማይለየው ጠባዩና የቆመበት መሰረቱ ነው።ልክ የሌለው ብዝበዛ ከሌለ፣ኢምፔሪያሊዝም የተባለ ጉድ የለም።

ግን እንዳልነው መልኩን ለውጦአል።ዛሬ ቀድሞ እንደሚበለው «ለእድገታችን ቅኝ ግዛት ያስፈልገናል፤...ኢምፔሪያሊዝም የተፈጥሮ ህግ ነው....» እያሉ መደንፋት ቀርቷል።የዛሬው ብዝበዛ የሚካሄደው በቀጥታ እንደቅኝ ግዛቱ ጊዜ ከውጭ ተሹመው በመጡ አስተዳዳሪዎች አይደለም።ከአገሩ ሰዎች ህዝባቸውን ከድተው ለባእድ የሚያድሩ ጥቂቶች እየተመለመሉ ነው።ዛሬ ተበዝባጋዥ አገሮች የራሳቸው ሰንደቅ አላማ፣የራሳቸው ሹማምንት... ወዘተ አሏቸው፤ግን በነዚህ አገሮች የኢኮኖሚ ሃይል የተያዘው በባእድ ባለሀብቶች ሲሆን በጠቅላላው የፖለቲክ አመራሩም የሚወሰነው በየመናገሻ ከተማዎቹ በሚገኙ

ት የኢምፔሪያሊስት አገሮች ኤምባሲዎች መሆኑ ግልፅ ነው።ብዝበዛው
ም የሚከሄደው እንደቀድሞው አይን እያወጣ ሳይሆን በእርዳታ፣በጋራ
ጥቅም፣በጋራ ፀጥታ፣... ወዘተ በሚሉት ባዶ ቃላት እየተሸፈነ ነው።ስለ
ሆነም የዛሬ ኢምፔሪያሊስቶች እርዳታ፣ትምህርት፣ፀጥታ፣መከላከያ ...
ወዘቱ እያሉ በየአገሩ ስር ቢሰዱ ዋናውና መሰረታዊው አላማ ብዝበዛ
ቸውን ለማጠንከርና ለመሸፋፈን ብቻ መሆኑን መረዳት አለብን።

ኢምፔሪያሊስቶች አላማቸው በፍፁም አልተለወጠም።ዛሬ
ም በተበዝባጋር አገሮች የሚፈልጉት አንደኛ ለፋብሪካ እቃዎች ገበያ፣
ሁለተኛ ለፋብሪካቸው የጥሬ እቃና ሶስተኛ ለገንዘባቸው ማሰሪያ ርካሽ
ጉልበትና ሀብታም አገር ነው።እነዚህንም አላማዎች ሲከታተሉ የተበዝ
ባጋር አገሮችን እድገትና እርምጃ እንደሚፃረሩ ለማየት አያዳግትም።ተ
በዝባጋር አገሮች የፋብሪካ ሸቀጥ ማራገፊያ እንደሆኑ እንዲቆዩ ከተፈለ
ገ በገዛ አገራቸው ፋብሪካ እንዳያቆሙ መደረግ አለበት።በጥሬ እቃ አቅ
ራቢነታቸውም እንዲረጉ ከተፈለገ ሀብታቸውን ከአገር ውስጥ ስራ ላይ
እንዳያውሉት መታገድ አለባቸው።ባጭሩ ቆዳ እየላኩ ጫማ ማስመጣ
ት፣ስኳር እየላኩ ከረሜላ ማስመጣት፣ብረት እየላኩ መኪና ማስመጣት
በኢምፔሪያሊስቶች የተበየነብን የእድገታችን ፀር ለመሆኑ የሚጠራጠ
ር ያለ አይመስለንም።ነገሩ «ከባልሽ ባሌ ይበልጣል፣ሽሮ አበድሪኝ» ነው
ኢምፔሪያሊስቶች ቆመው እንዲሄዱ ከተፈለገ የተበዝባጋር አገሮች እ
ድገት በፍፁም መገታት አለበት።

ዝቅ ብለን ባጭሩ ለመተንተን የምንሞክረው የኢፔሪያሊስ
ቶች ብዝበዛ ልዩ ልዩ መልኮች ሲ[illegible]፤ይህም ዘረፋ የተበዝባጋር አገ
ሮችን ህዝብ እድገት እንዴት እንደሚፃረረው ለማሳየት እንጥራለን።ይ
ህንንም በምናደርግበት ጊዜ በተቻለን መጠን የአገራችንን ምሳሌ ለመ
ስጠት እየሞከርን ነው።

በተበዝባጋር አገሮች ላይ የሚደገውን ዘረፋ መልክና ልኩ
ን ለመለየት እንዲቀል ዝርዝር ከመግባታችን በፊት አንዳንድ አጠቃላ
ይ አሳቦችን ለመስጠት እንወዳለን።

1ኛ. በተበዝባጋር አገሮች የሚገኙት የታላለቀ ጥሬ እቃዎች ም
ንጭ የተያዘው በኢፔሪያሊስቶች እጅ ሲሆን ስራ ላይ የ



ሚውለው ደግሞ ለነሱው ጥቅም ብቻ ነው።

2ኛ. ተበዝባጋር አገሮች ከሞላ ጐደል ንግዳቸውን የሚያከሂዱ
ት ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር ነው።የሚልኩትም ልዩ
ልዩ ጥሬ እቃዎችን ሲሆን የሚያስገቡት ደግሞ የፋብሪካ
እቃዎችን ነው።

3ኛ. በሁለቱ መካከል የሚደረው ንግድ የተዛባ ነው።ይህም ማ
ለት በኢንተርናሽናል ገበያ የጥሬ እቃ ዋጋ በየእለቱ ቁል
ቁል እየወረደ ሲሄድ የፋብሪካ እቃ ዋጋ ደግሞ በየእለቱ
እየጨመረ ይሄዳል።ከዚህ ንግድ ተበዝባጋር አገሮች የሚ
ደርስባቸው ኪሳራ በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

4ኛ. ኢምፔሪያሊስቶች ገንዘባቸውን ወደተበዝባጋር አገሮች እ
ያመጡ ሁለት አይነት ዘርፋ ያደርጋሉ።እነዚህም አንደኛ
በብድር ስም ለሚመጣው ገንዘብ የሚከፈለው ከፍተኛ ወ
ለድ ሲሆን፣ሁለተኛ ደግሞ በተበዝባጋር አገሮች ፋብሪካ እ
ያቋቋሙ የአገሪቱን ሰራተኛና ሀብት እየበዘበዙ የሚያግ
ዙት ትርፍ ነው።

5ኛ. በነዚህ ልዩ ልዩ ዘዴዎች ተበዝባጋር አገሮች በየአመቱ ከ
20 ሚልያርድ ብር በላይ ይዘረፋሉ።ብዙውን ጊዜ ተበዝባ
ጋር አገሮች ይህን እዳ በአንድ ጊዜ መክፈል ስለሚሳናቸ
ው ኢምፔሪያሊስቶች በእርዳታ ስም እንደገና በወለድ እ
ያበደሩ ይቀበሏቸዋል።

1. የጥሬ እቃዎች ምንጭና የኢምፔሪያሊስቶች ብዝበዛ

በተበዝባጋር አገሮች የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት ከኢም
ፔሪያሊስት አገሮች ሀብት ጋር ብናነፃፅረው ተበዝባጋር አገሮች ሲደኸዩ
የተፈጥሮ ሀብት በማጣት አለመሆኑን እናያለን።በትንሹ ለመገመት አን
ዳንድ ምሳሌዎችን ብንጠቅስ ከአለም የቤንዚን መጠባበቂያ ሀብት 75%፤
ከሚወጣው መዳብ 50%፤ከከባልት 75% የሚገኘው ከተበዝባጋር አገ
ሮች ሲሆን አልማዝን የወሰድን እንደሆነ ከ70% በላይ የሚወጣው ከ
ሶስት የአፍሪቃ አገሮች ሆኖ እናገኘዋለን።(1)

እነዚህና ሌሎችም ብዙ ጥሬ እቃዎች ለተበዝባዢ አገሮች የኢኮኖሚ እድገት መሰረታዊ ነገሮች መሆናቸው የታመነ ነው።ነገር ግን በየአገራቸው እንዳይሰራባቸው ወደኢምፔሪያሊስት አገሮች እየተወሰዱ የባእድ ኢኮኖሚ ሲያዳብሩ እናያለን።የኢምፔሪያሊስት አገሮች ኢኮኖሚ ቆሞ ለመሄድ የቻለው ከተበዝባዥ አገሮች በሚዛቀው ሀብት መሆኑን ለማሳየት አንዳንድ ምሳሌዎች እንጥቀስ።ኢምፔሪያሊስት አገሮች ለኢንዱስትሪያቸው ከሚያስፈልጓቸው ጥሬ እቃዎች ውስጥ ከተበዝባዥ አገሮች የሚያገኙት ስንት በመቶ ነው ብንል መዳብ 40%፣ካካዎ 100%፣ፔትሮል 50%፣ብረት 33%፣... ወዘተ. ሆኖ እናገኘዋለን።2 በዚህ አይነት ከተበዝባዥ አገሮች የሚጋዘው ሀብት በአገር ውስጥ ቢሰራበት ኖሮ ምን ያህል እርምጃ ይገኝ እንደነበረ ለመገመት አያቅትም። ዛሬ በድህነቱ ከኢትዮጵያ ሌላ ተወዳዳሪ የሌለውን የሳውዲ አረብያን ህዝብ ብንወስድ ብዙዎች ተመልካቾች እንደሚሉት በአለው የቤንዚን ሀብት ትላልቅ ኢንዱስትሪ ማቆም ይችል እንደነበረ ግልፅ ነው።ነገር ግን ከዚሁ አገር በሚጋዘው ቤንዚን የደረጁና የፋፉ የኬሚካል ኢንዱስትሪ ፋብሪካዎች የሚገኙት በምእራብ አገሮች ነው።

የእርሻን ስራ የወሰድን እንደሆነ የሚመረተው ሁሉ ለኢምፔሪያሊስቶች ገበያ ተፈላጊነት እንጂ ለአገሪቱ ህዝብ እድገትና መሻሻል አስፈላጊነቱ እየታየ አይደለም።ለምሳሌ በኢትዮጵያ ከ1961–66 ድረስ ለቡና ተክል የዋለው መሬት 40% ሲያድግ ለተራበው ህዝብ ምግብ ለሚሆኑ ሰብሎች የዋለው መሬት ስፋት የጨመረው በ5% ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን።(3) አልጀሪያ ቅኝ ግዛት በነበረችበት ወቅት ለወይን ተክል የዋለው መሬት በ300% ሲያድግ ለእህል የዋለው መሬት በ15% ቀንሷል ተብሎ ይገመታል።

ስለዚህ የማእድን ኢንዱስትሪውም ሆነ የእርሻው ተግባር የሚመራው በአገሪቱ ህዝብ ፍላጎት ሳይሆን በኢምፔሪያሊስቶች ገበያ ፍላጎት ነው ማለት ነው።ይኸም ሆኖ ታድያ ተበዝባዥ አገሮች የደከሙበትን ጥሬ እቃ ይዘው "ነፃ ገበያ" የሚሉት የኢምፔሪያሊስቶች ገበያ ሲደርሱ የተለየ ብዝበዛ ይጠብቃቸዋል።



2. የተዛባ ንግድና ተከታዩ ብዝበዛ

ተበዝባዥ አገሮች ምን ይዘው እንደሚቀርቡና ከሞላ ጎደል ንግዳቸውን ከማን ጋር እንደሚያካሂዱ ከፍ ብለን ጠቅሰነዋል።ከላይም እንዳልነው በዚህ ጊዜ የሚደረገው ይህ የተበዝባዥ ንግድ ከፍ ያለ ብዝበዛን ያስከትላል።ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር መነገድ ከተጀመረ አንስቶ ኢትዮጵያ ከቡና አቅራቢነት ደረጃ ወጥታ አታውቅም።ዛሬም ከውጭ ንግድ ከምናገኘው ሀብት 60%ው ከቡና ሽያጭ መሆኑን ማንም ያውቀዋል።በዚህም ንግድ የተሳሰርነው ከአንድ አገር ጋር ነው።ለምሳሌ እ.አ.አ. በ1968 እ.ም. 69590 ቶን ቡና ወደውጭ ስንልክ ሰስት አራተኛ የሚያህለው፣ማለት 50601 ቶን፣የተላከው ወደ አሜሪካ ነው (4)።ይህም እንግዲህ "በደንበኞቻችን" በአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ላይ ምን ያህል ጥገኛ እንደሆንን ያሳያል።

በአለም ገበያ ላይ የጥሬ እቃዎች ዋጋ ከቀን ወደቀን ቁልቁል እየወረደ ሲሄድ የፋብሪካ እቃዎች ዋጋ ደግሞ እየጨመረ መሄዱ ለማንም ግልፅ ነው።እ.አ.አ. ከ1945–1965 እ.ም. በዚህ በዋጋ መለዋወጥ ምክንያት ተበዝባዥ አገሮች ከሚልኩት እቃ 19% አጥተዋል (5)።ይህም ማለት በ1954 እ.ም. አንድ መኪና ለመግዛት 100 ኩንታል ቡና ያስፈልግ እንደሆነ እ.አ.አ. በ1965 እ.ም. ለዚህችው መኪና 119 ኩንታል ቡና ያስፈልጋል ማለት ነው።በዚህ የተዛባ ንግድ ኪሳራ ብቻ ከተበዝባዥ አገሮች በየአመቱ የሚወጣው ሀብት 15 ሚልያርድ ብር ይገመታል።(6)

ኢትዮጵያችንን ነጥለን ብንወስድ ይህን እውነት ከያለበት በተጠራቀሙ ቁጥሮች ለመረዳት እንችላለን።ወደአገር የሚገቡ እቃዎች ዋጋቸው የጨመረው እንዴት ነው? ወደውጭስ የሚላኩ እቃዎች ዋጋቸው እየቀነሰ የሄደው እንዴት ነው?

ባጭሩ፣ስንጠረጋ 1. እንደሚያመለክተው፣የምንገዛቸው እቃዎች ዋጋ እየጨመረ ሄዶአዋል።የምንሸጣቸው እቃዎች ዋጋ እየቀነሰ ሄዶአዋል።ከኢምፔሪያሊስቶቹ ገበያ የምናገኘው "ትርፍ" በየቀኑ እየጨመረ የሚሄድ ኪሳራ ነው ማለት ነው!! እንዲህ አርጐም ንግድ የለ!

ሰንጠረዥ 1.

ወደኢትዮዮያ ከውጭ የሚገቡ እቅዎችና ወደውጭ የሚላኩ አቃዎች
ዋጋ ያሳየው መለዋወጥ።(እ.አ.አ. የ1964 እንደመነሻ ተወሰደ) (7)

| አመት | 1964 | 1965 | 1966 | 1967 | 968 |
|---|---|---|---|---|---|
| ከውጭ የገቡ እቃዎች ዋጋ መለዋወጥ | 100 | 101.0 | 104.8 | 107.1 | 109.6 |
| ወደውጭ የተላኩ እቃዎች ዋጋ መለዋወጥ | 100 | 101.0 | 101.0 | 90.4 | 93.6 |

በተጨማሪ ደግሞ ዋናውን የንግድ እቃችንን ቡናን የወሰ
፦ን እንደሆን ነገሩ፣ በይበልጥ ለመረዳት እንችላለን።አሁንም የመንግ
ቱ እስታቲስቲክስ የሚያቅርብልንን ሂሳብ ወስደን እንመልከት።

ሰንጠረዥ 2.

ኢትዮጵያ ወደውጭ የላከችው ቡና ልክና የተገኘው ገቢ (8)።
(ከ1964–1966 እ. አ .አ)

| አመት | 1964 | 1965 | 1966 |
|---|---|---|---|
| የተላከ ቡና በሚልዮን ኪሎ | 70,22 | 87,7 | 73,6 |
| የተገኘ ገቢ በሚልዮን ብር | 15,88 | 18,82 | 15,57 |
| ገቢ በኪሎ(በግምት)፡በብር | 2,25 | 2,15 | 2,12 |

ባጭሩ በ1966 ወደውጭ የላክነው ቡና በ1964 ከላክነው
በብዛት ይበልጣል።ነገር ግን በ1966 ከቡና ሽያጭ ያገኘነው ገቢ በ1964
ካገኘነው ያነሰ ነው።አንበቢ ልብ ይበለው ከማለት በስተቀር እዚህ ላይ
ዝብዘባ አናበዛም።የዚህን ኪሳራ ግምት ለመስጠት ብቻ የሚከተለውን
ቁጥር እንጨምራለን።በ1065 አ.ም. (እ.አ.አ.) ኢትዮጵያ በዚህ የዋጋ
መውረድ ምክንያት 18 ሚልዮን ብር ለመተካት ከ77 ሚልዮን ኪሎግ
ራም በላይ ፍራፍሬና ከሁለት ሚልዮን ኪሎ በላይ ስጋና ከስጋ የተሰሩ



ምግቦች ወደውጭ ልከለች (9)።

### 3. በትርፍና በወለድ የሚዘረፈው ሀብት

ሌላው ብዝበዛ ደግሞ ኢምፔሪያሊስቶች በተበዝባጋ አገር
ች ገንዘባቸውን እያሰሩ የሚዝቁትና ወደአገራቸው የሚያሻግሩት ሀብ
ት ነው።ይህም ዘረፋ ሁለት አይነት መልክ አለው።አንዱ ዘረፋ ለተበዝ
ባጋ አገሮች በሚያበድሩት ገንዘብ የሚዝቁት ከፍተኛ ወለድ ነው።ሁለ
ተኛው ዘረፋ ደግሞ ፋብሪካ በማቋቋም የተበዝባጋ አገሮችን የተፈጥሮ
ና ሰብአዊ ሀብት እየበዘበዙ የሚያወጡት ትርፍ ነው።

በወለድ ስም የሚዘርፉትን ገንዘብ ለማሳየት ያህል አንዳን
ድ ቁጥሮችን መጥቀስ ይቻላል።ለምሳሌ በ1960 (እ.አ.አ.) የአፍሪቃ አ
ገሮች በብድርና በስጦታ ስም ከጠቅላላ ሀብታቸው 4% ያህል አግኝተ
ው ነበር።ነገር ግን በዚሁ አመት ከጠቅላላ ሀብታቸው 11% ትርፍ፣ወለ
ድ . . . ወዘተ. እየተባለ ወደኢምፔሪያሊስት አገሮች ተሻግሯል (10)።
ኢትዮጵያን የወሰድን እንደሆን በ1964 (እ.አ.አ.) በየምክንያቱ የተጠ
ራቀመበት ብድር ከ400 ሚልዮን ብር በላይ ሲሆን በዚሁ አመት በወለ
ድ ብቻ ወደውጭ የወጣው ሀብት ከ15 ሚልዮን ብር በላይ ነው(11)።

ሁለተኛው ዘረፋ ደግሞ ኢምፔሪያሊስት አገሮች በተበዝባ
ጋ አገሮች ገንዘባቸውን እያሰሩ የሚጨምቁትን ሀብት ይመለከታል።
በተበዝባጋ አገሮች የሰው ጉልበት ርካሽ ነው።ጥሬ ሀብት በገፍና በጥ
ሩ ዋጋ ይገኛል።ገበያም አለ።ስለዚህ ኢምፔሪያሊስቶች የሰው ጉልበት
ውድ ከሆነበትና ጥሬ እቃም እንደልብ ከማይገኝበት ሀገራቸው የሚያ
ገኙት ትርፍ አልበቃ ስለሚላቸው ወደተበዝባጋ አገሮች ይጉርፋሉ።
«ኢምፔሪያሊስቶች በመንገብገብ ወደ 3ኛው አለም (ወደተበዝባጋ ማለ
ታችን ነው) የሚፈሱት በዚሁ ርህራሄና ልክ በሌለው፣በዜሁ ምንም አ
ይነት ሀላፊነት በማያስከትለው ዘረፋ እየተሳቡ ነው እንጂ ልክ ላለው ዘ
ረፋማ አገራቸው ምን አላቸው ነበር?በአገራቸው ከልዩ ልዩ የሶሻል፣የ
ፖለቲካና የኢኮኖሚ ምክንያቶች የተነሳ ከዘረፋ የሚገኘው ገቢ እየተ
ቀነሰባቸው ስለሄደ አይደለም? ወደኛ ሲመጡ ግን ልክ ለሌለው ዘረፋ የ
ተመቻቸ ገነት ሆኖ ያገኙታል . . . »(12)።ለዚህ ምሳሌ በአገራችን የቢ.
ኤን. የስኳር ፋብሪካን መጥቀስ ብቻ ይበቃል።እነዚህ የባእድ ካፒታሊ

ስቶች ወደኢትዮጵያ ሲመጡ ቋጥረው የመጡት ሀብት እናቷም እባቷ
ም 22,400,000 ብር ነበረች።በመጀመሪያ የያዙትን መሬት መንግስቱ
ለ90 አመት ፈቀደላቸው።የመሬቱም ኪራይ በጋሻ በአመት 1 ብር ብቻ
ነበር።ስራ ከጀመሩ አንስቶ እስከአምስት አመት ድረስ ምንም አይነት ቀ
ረጥ እንዳይከፍሉ ተፈቅዶላቸው ነበር(13)።በዚህ ላይ መንግስቱ የወን
ጂ ስኳርን እድገት ለመጠበቅ ከውጭ የስኳር ነጋዴዎች ቶክከር ሊከል
ለው ቃል ገብቶ ስለነበረ ተወዳዳሪ የሌለው ከፍተኛ ዋጋ ለመወሰን ቻ
ለ።በዚህም በኩል ድሃው ህዝብ ተበዘበዘ።አሆጂ የተባለው ፀሀፊ በዚህ
ጉዳይ እንዲህ ብሎ ፅፎዋል።«ምንም እንኳን በአለም ገበያ የስኳር ዋጋ
ቢወድቅና የቀረጥ ምህረቱም ወቅት ቢያልፍ ኤች. ቪ. ኤ. በ1959 እ.
ም. (እ.አ.አ.) 7.4 ሚልዮን ብር የተጣራ ትርፍ አግኝቷል»(14)።ይህ
ም ማለት በአገሩ ስኳር የሚሰራለት የኢትዮጵያ ድሃ የሚያስፈልገውን
ስኳር የሚያገኘው ከአለም ገበያ በላይ በሆነ ዋጋ ነው ማለት ነው።የስኳ
ር ዋጋ ቀድሞ ከውጭ ከምናስመጣበት ጊዜ ጋር ሲነፃፀር ዛሬ ይበልጥ
መወደዱን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም።

ይህ ትርፍ የሚገበሰበሰው እንግዲህ ከብዙ ወገን ነው ማ
ለት ነው።እዚህ ግባ በማይባል የቀን ደመወዝ (ከአንድ ብር በታች) የ
ሚበዘበዘው የኢትዮጵያዊያን ጉልበት አለ።ከዚያም ለባእድ ጥቅም ስራ
ላይ የሚውለው የአገራችን የተፈጥሮ ሀብት አለ።የግፍ ግፍ በእንቅርት
ላይ ጆሮ ገድፍ ነውና እንዲህ በዘረፋ የተገኘውን ስኳር ደግሞ የኢት
ዮጵያ ህዝብ በመሉ ከአለም ገበያ በላይ በሆነ ዋጋ እንዲገዛ ይገደዳል።

ይህም ሁሉ ሆኖ የተገኘው ትርፍ በሀገሪቱ ቢሰራበት አን
ድ ተስፋ ነበር።ነገር ግን የውጭ ባለገንዘቦችን "ለማበረታታት" የወጣው
የ1963(እ.አ.አ.) ህግ በአንቀፅ 8 በየአመቱ የሚገኘውን ትርፍ፣ከውጭ
የተበደሩትን ገንዘብና ወለድ ለመክፈል፣የውጭ ዜጋ ሰራተኞች ያጠራቀ
ሙትን ሀብት ለማውጣት፣ለመጓጓዝ ... ወዘተ. እየተባለ ልክ የሌለው
ሀብት ከአገሪቱ እንዲወጣ ይፈቅዳል።

ባጭሩ የዛሬ 20 አመት ግድም 22 ሚልዮን ብሩን ቋጥሮ
የወጣ የባእድ ኩባንያ እስከዛሬ ድረስ ከአገራችን ያጋዘውን ሀብት አን
ባቢ እንዲገምተው ትተነዋል።ተበዝባጋ አገሮች ዋና ችግራቸው የካፒ



ታል እጥረት ነው እያሉ ለማጭበርበር የሚሞክሩ ሞልተዋል።ነገር ግን
ከፍ ብለን የጠቀስነው ሂሳብ እንደሚያስረዳን ለነዚህ አገሮች ለእድገታ
ቸው ዋና እንቅፋት የካፒታል እጥረት ሳይሆን በኢምፔሪያሊስቶች መ
በዝበዛቸው ነው።

## 4. እርዳታና ብዝበዛ

ከላይ የዘረዘርናቸው ልዩ ልዩ ዘረፋዎች በአንድነት ሲጠቃ
ለሉ ተበዝባጋ አገሮች በየአመቱ ከ20 ሚልያርድ ብር በላይ ወደኢም
ፔሪያሊስት አገሮች እንዲያሻግሩ ይገደዳሉ ማለት ነው(15)።ይህን ያህ
ል ገንዘብ በየአመቱ ለመክፈል ተበዝባጋ አገሮች በጣም ይሳናቸዋል።
ስለዚህም ኢምፔሪያሊስቶች ይህን ዘረፋቸውን በይበልጥ ለማደርጀት ያ
ገኙት ዘዴ "እርዳታ" የሚሉት ፈሊጥ ነው።"እዳቸውን" መክፈል የተሳ
ናቸውን ተበዝባጋ አገሮች "በእርዳታ" ስም ገንዘብ እያበደሩ መልሰው
እሱኑ ይቀበሏቸዋል።

ኢምፔሪያሊስቶች እንደዚህ "እርዳታ" የሚሉት የነሱኑ
"እዳ" ለመክፈል እንድንችል በከፍተኛ ወለድ የሚያበድሩንን ገንዘብ ነ
ው።ሁለተኛ ደግሞ እርዳታ የሚሉት ገበያ ያላገኙለትን ሸቀጥ ተበዝባጋ
አገሮች ላይ ለማራገፍ እንደዚሁ ለእቃ መግዣ በወለድ የሚያበድሩት
ን ገንዘብ ነው።ዛሬ እንዲያውም ከሚገኘው እርዳታ ብዙው የሚውለ
ው የቀድሞውን ብድር ከነወለዱ ለመክፈል እየሆነ ሄዶአል።

<u>*መደምደሚያ:*</u>

በተበዝባጋ አገሮች የእርምጃ ቁልፍ የተያዘው በኢንዱስ
ትሪ መስፋፋት ብቻ መሆኑን ሁሉም የሚያምንበት ነው።ማንም አገር ባ
ለው ሰብአዊና የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅሞ ወደፊት ለመራመድ እንዲች
ል ከተፈለገ ከባድ ኢንዱስትሪ መስፋፋት አለበት።ኢምፔሪያሊስቶች ግ
ን ይህን አይፈቅዱትም።ተበዝባጋ አገሮች ይህን መንገድ ቢከተሉባቸ
ው ቀልጠው እንደሚቀሩ ያውቃሉና።ዋና ፍላጐታቸው ተበዝባጋ አገ
ሮች የነሱ ኢኮኖሚ "ተቀፅላ" በመሆን የፋብሪካ ሸቀጥ ማራገፊያ፣የጥሬ እ
ቃ ምንጭ፣የሀብት ማከማቻ መስከ ሆነው ዘልአለማቸውን እንዲቀሩ ነ

ው።ተበዝባዥ አገሮች፣ወደኋላ ያስቀራቸው ለኢምፔሪያሊስት አገሮች ኢኮኖሚ ተቀፅላ ሆነው መበዝበዛቸው ነው።

የኢምፔሪያሊስት አገሮች ቆመው ለመሄድ ምን ያህል በተበዝባዥ አገሮች ላይ እንደተጫኑ አይተናል።የብዝበዛውንም ልክና ልዩ ልዩ መልኮች በመጠኑ ተመልክተናል።ተበዝባዥ አገሮች ከድህነት፣ ከበሽታና ከድንቁርና ለመላቀቅ ከዚህ አፋኝና በዝባዥ ከሆነ ጥገኝነት ፈፅመው መላቀቅ አለባቸው።በኢምፔሪያሊዝም አለም እስከታሰሩ ድረስ ብዝበዛ ደካማነትን፣ደካማነት ብዝበዛን እያስከተለ ድህነት፣በሽታና ድንቁርና እየተስፋፋ ይሄዳሉ።በኢምፔሪያሊዝም ስር ሆነው ተበዝባዥ አገሮች ምንም አይነት የእድገት ተስፋ የላቸውም።ፔር ዣሌ እንዳለው ሁሉ «የተበዝባዥ አገሮች እድገት በኢምፔሪያሊስቶች ታፍኖ ተይዟል።ይህ ብዝበዛ ተሰባብሮ ካልወደቀ ምንም አይነት መውጫ የለም።የተበዝባዥ አገሮች ህዝቦች ሌላ መንገድ የላቸውም።ይህን ግንኙነት ሰባብረው ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ለመቆራረጥ መታገል አለባቸው።ነገር ግን ኢምፔሪያሊዝምም ሌላ ምርጫ የለውም።እንደዚህ አይነቱ መቆራረጥ ለተበዝባገሮቹ የቀራቸው አንድ የህይወት በር ሲሆን ለበዝባገሮቹ ደግሞ የሞታቸው ዋዜማ መሆኑ ነው።ሁለቱን ለማስታረቅ በፍፁም አይቻልም»(16)።

ህዝቦች ወደፊት ለመራመድ ከፈለጉ ከሁሉ አስቀድሞ ኢምፔሪያሊዝምና በየአገሩ ከሱ ጋር ተሳስረው የሚዘርፉት ቱጃሮች ሁሉ ደምስሰው ማጥፋት አለባቸው።የነዚህ ፀረህዝቦች የፖለቲካና የኢኮኖሚ ህይላቸው መሰበር አለበት።ለዚህም የተበዝባዥ አገር ህዝቦች ተደራጅተው በመነሳት ለቢሄራዊ ነፃነት፣ለህዝባዊ መንግስትና ከዚያም ለሶሺያሊዝም መታገል አለባቸው።

---

(1) P. JALLÉ "L' IMPERIALISME EN 1970" Petite Collection Maspero. ከልዩ ልዩ ገፆች የተውጣጣ ቁጥር።
(2) –"– ከላይ ከተጠቀሰው መፅሀፍ ከልዩ ልዩ ገፆች የተውጣጣ



(3) የኢትዮጵያ አመታዊ ስታቲስቲክስ መፅሄት ከ1965 ገፅ 48 ከ1966 አመታዊ መፅሄት ገፅ 46 የተውጣጣ።
(4) የኢ.ት. አመታዊ ስታቲስቲክስ መፅሄት የ1966 ገፅ 125
(5) P. JALLÈ Op. Gt. ገፅ 60
(6) Charles Bettelheim: Planification et croissance accèlérée. Petite collection Maspero ገፅ 38
(7) የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በየሶስት ወር የሚወጣ መፅሄት መስከረም 1962 ቁጥር 23 (81) ከገፅ 32 እና 33 የተገኘ።
(8) አመታዊ የስታቲስቲክስ መፅሄት 1966 ከገፅ 114 የተለቀመ
(9) —"— " —"— " —"— " —"— 113 የተገኘ።
(10) P. JALLÈ: Le PILLAGE du tiers monde Cahiers libres No. 68 F. Maspero ገፅ 86.
(11) Ethiopian Observer Vol. X No. 4 pp. 317-318:
(12) "ትግላችን" ግንቦት-ሰኔ 1961 ቁ. 3 "ተፈጥሮን በተመክር?" ገፅ 43
(13) Development and legislation in Ethiopia K. AHOOJA Ethiopian ObServer Vol. X No. 4 pp. 278
(14) Ibid. 278.
(15) Charles Bettelheim Op. Gt. pp. 40
(16) P. JALLÉ "L' IMPÉRIALISME EN 1970 pp. 176

## እድገትና የእድገት ችግሮች

ዛሬ የምንገኝበት አለም በሁለት ተከፍሎ እናየዋለን፤በአንድ በኩል በካፒታሊስት ስርአትና አቋም የሚተዳደሩት አገሮች፣በሌላው በኩል ደግሞ በሶሽያሊስት ስርአትና አቋም የሚተዳደሩት አገሮች። "ሶስተኛው አለም" ተብሎ "የሚጠራው" ክፍለ-አለም ልዩ ስርአት፣ልዩ የአስተዳደር አቅድና ርእዮተ አለም የለውም።የካፒታሊዝም ክፍለ-አለም ሆነው ከልክ በላይ በኢምፔሪያሊዝም እየተበዘበዙ በድህነት ጭቃ ውስጥ የሚዳክሩትን አገሮች አጠቃልሎ የሚዘው ክፍል ነው።

ከእነዚህ አገሮች አብዛኞቹ ከጥቂት አመታት በፊት በቅኝ አገዛዝ ስር ነበሩ፤ዛሬ ደግሞ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት በመሆን በኢምፔሪያሊዝም የሚበዘበዙ ናቸው።ሁኔታቸውን አይነተኛ የሚያደርገው አንዱ ይህ ሲሆን፤ሁለተኛው ደግሞ ጠቅላላ ሀብታቸው (ኢኮኖሚያቸው) ከሌሎች አገሮች ጋር ሲተያይ ወደኋላ የቀረ መሆኑ ነው።ከዚህም የተነሳ ምእራባዊያን የልማት ሊቆች (ኢኮኖሚስቶች) "ወደኋላ የቀሩ" ወይም "ያልበለፀጉ" አገሮች ብለው ይጠሯቸዋል።ይህ አጠራር እነዚህ አገሮች የሚገኙበትን ሁኔታ አብራርቶ የማያሳይ ከመሆኑም በላይ "ኢኮኖሚያቸው የሳሳበትንም" እውነተኛ ምክንያት በትክክል አያመለክትም። አለም በእድገት ጐዳና ላይ ሲራመድ እነዚህ አገሮች "ወደኋላ ቀርተዋል" ብሎ መዝጋት አህያውን ትቶ ዳውላውን እንደማለት ነው።

በታሪክ በኩል የተመለከትነው እንደሆን እነዚህ አገሮች እድገታቸው ተደናቅፎ በሚገባ ያልተራመዱት፣መጀመሪያ በቅኝ አገዛዝ ቀጥሎም በእጅ-አዙር ቅኝ አገዛዝ "ኢምፔሪያሊስት" ሀይልች የጥሬ እቃ መዛቂያቸው ምንጭ፤የሸቀጣ ሸቀጣቸው ማራገፊያ ገበያ፤የካፒታላቸው ማራቢያ መስክ በማድረግ ሲጠቀሙባቸውና ሀብታቸውን ሲዘርፉ በመቆየታቸው ነው።በኢኮኖሚ ረገድ የተመለከትነው እንደሆን፤ኢምፔሪያሊስት ሀይሎች እነዚህን አገሮች ጥገኛ እንዲሆኑ በማድረግ ሀብታቸውና የጉልበታቸው ፍሬ ሁሉ ለራሳቸው ብልፅግና ሳይውል ለኢምፔሪያሊስቶቹ የኢኮኖሚ ድጋፍ ወይም ማሕያ እንዲሆን በማድረጋቸው ነው።በፖለቲካ ረገድ ደግሞ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑት ኢምፔሪያሊስቶች



በነዚህ አገሮች ውስጥ በስልጣን ላይ ያሉትን ከዳተኞች በጥቅም አስረው በሀይላቸው ደግፈው በመያዝ ጊዜው የተላለፈና የበሰበሰ ህብረተሰባዊ አቋምና አገዛዝ እስከዛሬ እንዲቆይ በማድረጋቸው ነው።በጠቅላላው እነዚህ አገሮች ያልበለፀጉበት፣የእድገት እርምጃቸው እንደሌሎች አገሮች ያልተፋጠነበት ምክንያት የተራመዱት ኢምፔሪያሊስት አገሮች የእድገታቸው እንቅፋት በመሆን በብዝበዛ ቀንበር ውኃጥ ስላገቡዋቸውና ዛሬም አፍነው ስለያዙዋቸው ነው።ስለዚህም፣ይህን መሰረታዊ እውነት ባለመዘንጋት "ወደኋላ የቀሩ አገሮች" ወይም "ሶስተኛው አለም" ከማለት "ተበዝባዥ አገሮች" ማለቱ ትክክለኛ ሁኔታቸውን ይገልፃል ብለን እናምናለን።በሚቀጥለው ፅሁፋችንም ውስጥ "ተበዝባዥ" በሚለው ቃል እንጠቀማለን።

ኢትዮጵያ ከነዚህ አገሮች አንዷ ነች።በጊዜያዊው ታሪኳ፤አሁን ባለችበትም ሁኔታ ሆነ በወደፊት እድልዋ (የችግሮችዋ መፍትሄ) በመሰረቱ ከነዚህ ተበዝባዥ አገሮች ነጥለን ልንመለከታት አንችልም።ስለዚህም መጀመሪያ "ሶስተኛ አለም" ተብሎ የሚጠራውን ተበዝባዥ አለም በጠቅላላ በመወለድ ያለበትን ሁኔታና የእድገት ችግሮቹን እንመለከታለን።ቀጥለን፤በተለይ የኢትዮጵያ ሁኔታና የእድገት ችግሮች ለመተንተን እንሞክራለን።በመጨረሻም ለእድገት ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉትን "ቀዳማዊ ነገሮች" ለማመልከት እንሞክራለል።

### I. ተበዝባዥ አለምና ኢምፔሪያሊዝም

"ሶስተኛ አለም" በሚባለው ክፍል ውስጥ ተጠቃልለው የሚገኙት ተበዝባዥ አገሮች በህዝብ ብዛት የአለምን ሁለት ሶስተኛ የያዙ ናቸው።እነዚህ አገሮች ያሉበት ሁኔታ በሶስት ታላላቅ አርእስቶች ስር ሊጠቃለል ይችላል።እነዚህም፤አንደኛ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ረገድ ጥገኞች ናቸው፤ሁለተኛ በልዩ ልዩ መንገድ ይበዘበዛሉ፤ሶስተኛ የኢኮኖሚ እድገታቸው በልዩ ልዩ ሀይሎች ተቋርጦና ተሰናክሎ ይገኛል።

#### 1ኛ ጥገኝነት

##### ሀ) የፖለቲካ ጥገኝነት

የጥገኝነት የመጨረሻው ከፍ ያለው መልኩ ቅኝ ግዛት ሲ

ሆን ዛሬ ከሚበዘበዙት አገሮች አብዛኞቹ ይህን አይነቱን ባርነት ቀምሰ
ዋል።አንዳንዶቹም ገና በዚሁ ግዛት ስር ይገኛሉ።በቅኝ ግዛት የተያዙ አ
ገሮች ብሄራዊ ሀብታቸው ያለአንዳች-ገድብ በወራሪው ሀይል ይዘረፋ
ል።የንግዱ ግንኙነት መቶ በመቶ ከወራሪው አገር ጋር ብቻ ሲሆን የን
ግዱም እቃና ሸቀጥ የሚጓጓዘው በወራሪው አገር የመገናኛ መስመሮ
ች ብቻ ነው።

ዛሬ የቅኝ ግዛት ከነበሩት አብዛኞቹ አገሮች "በስም"ብቻ ነ
ፃነታቸውን አግኝተዋል።ነገር ግን ከሞላ ጎደል ሁሉም በእጅ-አዙር-አ
ገዛዝ ስር ይገኛሉ።ይህም ማለት ጥገኝነቱ እንደበፊቱ መቶ በመቶ መ
ሆኑ ቀርቶ ትንሽ ላላ ብሎ እናየዋለን ማለት ነው።ያገሩ ሰዎች "ተመል
ምለው" አስተዳዳሪዎች ሆነዋል፤ቅኝ ግዛት በነበረችበት ጊዜ በቀጥታ ጥ
ሬ እቃዋን በሙሉ ለወራሪው ሀይል ብቻ ለመሸጥ፣ከፋብሪካ የወጡ ሸ
ቀጣ ሸቀጦችን፣ደግሞ ከዚያው ሀይል ብቻ ለመግዛት ትገደድ ነበር፤አሮግ
ጥ ዛሬም የንግድ ግንኙነት ይበልጡን ከዚያው አገር ጋር ሲሆን በጥቂ
ቱ ደግሞ ከሌሎች አገሮች ጋር መነገድ ይቻላል (ይኖራል)።ለአንድ ጌ
ታ ብቻ በማደር ፈንታ ለሁለት፣ሶስት.. ወዘተ. ጌታዎች ማደር ይቻላል
ማለት ነው።አልፎ አልፎ ከጌታ ጌታ ማማረጥም ይቻል ይሆናል።በተበ
ዝባጋር አገሮች ውስጥ በስልጣን ላይ "የተቀመጡት" መደቦች ከውጭ
ካፒታሊስት ሞኖፖሎች ጋር በጥቅም በመተሳሰር አገሪቷ ከኢምፔሪያ
ሊስት ጥላ ስር እንዳትወጣ ያደርጋሉ።በኢምፔሪያሊስት ሀይሎች ድጋ
ፍ የነዚህ መደቦች <u>በስልጣን ላይ መኖር ራሱ</u> (እቅዳቸው ሁሉ ለግል ጥ
ቅም ነውና) ለብሄራዊ ልማት ጠንቅ ሲሆን በተጨማሪ ደግሞ ማነኛው
ም የኢኮኖሚ እድገት የተዛባ መልክ እንዲይዝና ጥገኛ ሆኖ እንዲቀር
ያደርገዋል።ኢምፔሪያሊስትም ሆኑ ብሄራዊ ባለስልጣኖች ጊዜው የተላ
ለፈበት ስርአትና አቋም በአገሪቱ ውስጥ ተጠብቆ እንዲቆይ መድከማቸ
ው ሲታወቅ ይህ ጥረት የሚያስከትለውን "የልማት እንቅፋት" መገመ
ት አያዳግትም።ለምሳሌ ባላባታዊ ወይም የፊውዳል ስርአት ተጠብቆ በ
ሚቆይበት ጊዜ ራሱን የቻለና ነፃ የሆነ ብሄራዊ የነጋዴና የፋብሪካ መደ
ብ እንዳያድግ እንቅፋት ይሆንበታል።የሚፈጠሩት ነጋዴዎችና ባለፋብ
ሪካዎች ሁሉ ከውጭ ሞኖፖሎች ጋር በጥቅም የተሳሰሩ በመሆናቸው



ከጥገኝነት አልፈው ብሄራዊ የእድገት ሀይል ሊሆኑ አይችሉም።

እንደዚህ ያለው የፖለቲካ ጥገኝነት የኢኮኖሚ ጥገኝነትን
ከሚያጠነክሩት ነገሮች ዋናው ነው።

ሀ) <u>የኢኮኖሚ ጥገኛነት</u>

የኢኮሚ ጥገኛነት ብዙ አይነት መልክ ሲኖረው የሚያስከ
ትለው የአገሪቱን ኢኮኖሚ የተዛባ እድገት ነው።

በውጭ ንግድ በኩል የተመለከትን እንደሆን የአገሪቷ የው
ጭ ንግድ በአንድ ወይም በሁለት እቃ ላይ ብቻ ተመስርቶ፣ይህም እቃ
ወደአንድ ወይም ቁጥራቸው ወደተመጠነ አገሮች ብቻ ሲላክ እናያለን።
ይህም ማለት የአገሪቷን ኢኮኖሚ ቆሞ እንዲሄድ የሚያደርገው፤የእድ
ገቷን ፍጥነትና አይነት የሚወስነው ይህ እቃ "በተመጠኑት" ደንበኞች
ዋ ገበያ ላይ የሚኖረው ዋጋ ነው ማለት ነው።

እንደዚህ ያለው ግንኙነት ተበዝባጋር አገሯን ጥገኛ ከማድ
ረጉም በላይ የኢኮኖሚ እድገቷ የተዛባ እንዲሆን ያስገድደዋል።ሀብቷ
ሁሉ በአንድ የንግድ እቃ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ይህን እቃ የሚያ
ፈራው የኢኮኖሚ ክፍል ብቻ እንዲዳብር ይሆንና የቀረው ሁሉ እንደ
ቆመ ይቀራል።ይህንን በብዝበዛ ላይ የተመሰረተ ንግድ የሚያገለግሉ ከ
ተሞች፣ወደቦች፣የመገናኛ መስመሮች ... ወዘተ. ሲበለፅጉ ሌላው ክፍ
ል አይነቃነቅም።

2ኛ. <u>የብዝበዛ አይነት</u>

ተበዝባጋር አገሮች ወደኋላ ያስቀራቸው ዋናው ምክንያት በ
ኢምፔሪያሊስት አገሮች መበዝበዛቸው ነው።ዋነኛ አድርጎ የያዛቸው
በዝባጋር ሀይል ደህንነቱና ብልፅግናው በትርፍ ላይ-የተመሰረተ ሲሆን
ዋና ጥረቱም የትርፍ ቦታ ማግኘት ነው።ስለዚህም ጥቅሙ አስገድዶት
የራሱን እድገት በሶስተኛው አለም ብዝበዛ ላይ መመስረቱ አያስገርመ
ንም።የሚያስደንቀን ይህን ብዝበዛውን ለማፅደቅ የሚያቀርበው ማጭበ
ርበርያ (እርዳታ፣የጋራ ድጋፍ ... ወዘተ.) ወደመቃመን መድረሱ ነው።

ሀ) <u>በገንዘብ ላይ የተመሰረተ ብዝበዛ</u>

እንደዚህ አይነቱ ብዝበዛ የሚካሄደው <u>የባእድ ካፒታል</u> በ

የአገሩ ገብቶ ትርፍ እንዲያፈራ በሚደረግበት ጊዜ ነው።ይህ ካፒታል በየአመቱ ለባእድ ካፒታሊስቶች የሚያስገኘው ትርፍ ከፍተኛ ሲሆን ከዚህም ይበልጡ ወደአገራቸው የሚያግዙት ነው።ወደአገራቸው ተመልሶ የሚሄደው ካፒታሉ ብቻ ሳይሆን ትርፉ ጭምር ነው።በ1966ና 1967 እ.ም. (እ.አ.አ.)፣በአንድ አመት ውስጥ፣የውጭ ካፒታል በትርፍ መልክ በትንሹ አምስት ሚልያርድ የአሜሪካን ብር ከሶስተኛው አለም ወሰዷል (1)።

ለ) <u>በንግድ ላይ የተመሰረተ ብዝበዛ</u>

ተበዝባጋር አገሮች ከኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር የሚያደርጉት ንግድ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ወይም የጋራ ጥቅሙ የተመዘዘነ ሳይሆን ለበዝባጋር አገሮች የሚበጅና ለነሱ ብልፅግና የተስማማ ነው። የንግዱ ግንኙነት የተመሰረተው ኢምፔሪያሊስቶች በደለደሉት አለም አቀፍ የስራ ክፍያ ላይ ነው።

1. በኢንዱስትሪ የዳበሩት በዝባጋር አገሮች ላልበለፀጉት አገሮች <u>በንግድ መልክ</u> ከሚሸጡላቸው አራት አምስተኛው ከፋብሪካ የወጣ ሸቀጣ ሸቀጥ ሲሆን የነዚህ እቃዎች ዋጋ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ሲሄድ እናየዋለን(2)።እነዚህ የውጭ ሞኖፖሎች በተበዝባጋር አገሮች ላይ ከፍ ያለ ተፅእኖ ስላላቸው የአገሮቹ መሪዎች የነዚህ ሞኖፖሎች እቃ ብቻ እንዲገባ ያደርጋሉ፤በተጨማሪ ደግሞ በዝባገሮቹ እነዚህን "ድሃ" አገሮች በንግድ ውል እያሰሩና በገንዘብ ክልል (ዞን) ውስጥ እያስገቡ ተመሳሳይ "የሞኖፖል ውጤት" ያስገኛሉ።እንደዚህ "የታሰሩት" አገሮች ከሌላ ገበያዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በጣም የተወሰነ ይሆናል ማለት ነው።

2. ተበዝባጋር አገሮች ወደውጭ ከሚልኩት የንግድ እቃ ዘጠኝ አስረኛው ጥሬ እቃ ሲሆን በኢምፔሪያሊስቶች "አለም-አቀፍ ነፃ ገበያ" ላይ የነዚህ እቃዎች ዋጋ ከጊዜ ወደጊዜ እየወደቀ ሲሄድ ይታያል(3)። እንደዚህ ባለው በተዛባ ንግድ ተበዝባጋር አገሮች ከአመት ወደአመት ጉዳታቸውና ኪሳራቸው እየጨመረ ከመሄድ አቋርጦ አያውቅም።ይህ ኪሳራ በየአመቱ ከሁለት እስከ ሶስት ሚልያርድ የአሜሪካን ብር ሲሆን እ.አ.አ. ከ1954 እስከ 1965 እ.ም. 19% ጨምሯል(4)።ማለትም፣ለምሳሌ ኢትዮጵያ በ1954 አንድ የእርሻ መኪና ለማስመጣት 100 ኩንታል ቡና መላክ እንደነበረባት በ1965 ያንንው መኪና ለማስመጣት 119 ኩንታል ቡና መላክ ነበረባት ማለት ነው።ዛሬ ደግሞ ከዚህም እንደሚበልጥ አይጠረጠርም።ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በምናደርገው የውጭ ንግድ ምክንያት፣ብሄራዊ እድገታችንን ለማፋጠን የምናደርገው ጥረት ሁሉ፣በዚህ አይነት፣ዋጋ ቢስ ሆኖ ይቀራል ማለት ነው።

3ኛ. <u>የኢኮኖሚ እድገት መቋረጥ (መታፈን)</u>

ከዚህ በላይ ባጭሩ ባቀረብነው ትንተና በበዝባጋርና በተበዝባጋር አገሮች መካከል ያለው የበላይና የበታች ግንኙነት "ሶስተኛውን አለም" ጥገኛ በማድረግና በልዩ ልዩ መንገድ በመበዝበዝ ለእድገቱ እንዴት እንቅፋት እንደሆነው አመልክተናል።አሁን ደግሞ ይህ "የኢኮኖሚ እድገት" እንዴት ታፍኖ እንደተያዘ ለማየት እንሞክር።

ሀ) <u>እድገትን የሚገቱ የውጭ ሀይሎች</u>

የውጭ ካፒታል በትርፍ መልክ "ከሶስተኛው አለም" የሚጨምቀውና በንግድ በኩል የሚያተርፈው ሀብት ባንድነት ተደምሮ በአመት ዘጠኝ ሚልያርድ የአሜሪካን ብር ይደርሳል ተብሎ ይገመታል። ይህም ቢታሰብ እያንዳንዱ "የሶስተኛው አለም" ተወላጅ በአመት አራት የአሜሪካን ብር ተኩል ለበዝባጋር አገሮች ይከፍላል ማለት ነው(5)። ይህ ሁሉ ተጠራቅሞ ለእድገት ቢያገለግል ኖሮ ለእድገት ሊውል የሚችለውን የሃብት ልክ በ75% ከፍ ያደርገው ነበር።

ይህንን ኪሳራና ጉዳት ለመሸፈን በእርዳታ ስምና በብድር መልክ ኢምፔሪያሊስት ሀይሎች "ለሶስተኛው አለም" ገንዘብ እንደሚሰጡ እናውቃለን።በዚህ ረገድ ልናስተውላቸው የሚገባን አንዳንድ ነገሮች አሉ።

—እንደዚህ ያለው እርዳታ ዘጠኝ አስረኛው ከመንግስት ወደመንግስት በግል የሚሰጥ ሲሆን አንድ አስረኛው ብቻ በአለም-አቀፍ ድርጅቶች በኩል ያልፋል(6)።የመጀመሪያው <u>አይነት እርዳታ ሊያስከትል የሚችለው</u> ታዛጋርነት አይዘነጋም።ሁለተኛውም አይነት "ልገሳ" ለስሙ በአለም-አቀፍ ድርጅቶች አማካይነት ይባል እንጂ እነዚህ ድርጅቶች የ

ሚከሄዱትና የሚታዘዙት በአንዳንድ ኢምፔሪያሊስት ሀይሎች መሆናቸው አይሳትም፤ለምሳሌ በአለም ባንክ አሜሪካ የያዘውን ቦታ ማስታወስ ይበቃል።

—በጠቅላላ አነጋገር ኢምፔሪያሊስት ሀይሎች ለብዝበዛቸው የሚመቻቸው ተበዝባገር አገሮች እንደተዳከሙ ሲቆዩላቸው ነው።ለዚህም እርዳታ እየተባለ የሚሰጠው ገንዘብ ከበጐ ፈቃድ የመነጨ ሳይሆን የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ለመጠበቅ የተፈጠረ ብልሃትና "ድሀ" አገሮችን በለበት ለማስረገጥ የተተለመ እቅድ ነው።በየአመቱ በርዳታና በብድር ስም የሚሰጠው ገንዘብ ድምር፣ኢምፔሪያሊስቶች ከሶስተኛው አለም በትርፍ መልክ ከሚዘርፉት ሀብት ያነሰ መሆኑ ይታወሳል።ይህ እርዳታ ባይኖር፡ ኖሮ፡ 1) ትርፋቸውን በውጭ ገንዘብ ወደአገራቸው መልሰው መውሰድ አይችሉም ነበር፤ 2) በተበዝባጋር አገሮች ውስጥ የኢምፔሪያሊስት ሎሌ የሆኑት መሪ መደቦች በስልጣን ላይ መቆየት አይችሉም ከዚህም የተነሳ የሚደረገው "እርዳታ" ሁሉ የመንግስቱን የእለት ችግር ለማቃለልና የበዝባጋር አገሮችን ሀብት ለማዳበር እንጂ ለአገሪቷ ብልፅግናና ለህዝቡ ደህንነት ታስቦ አይደለም።

—ይህ እርዳታ ከአመት አመት ጠቅላላ ቁጥሩ ጥቂት ሲጨምር ቢታይም "ከመፅዋቾቹ" የሀብት እድገት ጋር ሲተያይ እንዲያውም እየቀነሰ ነው የሚሄደው፤የጠቅላላ ገቢያቸውን 1% እንኳ አይሆንም።ይህንንም እርዳታ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ህዝቦች፣በግብር ስም ሲከፍሉ ኢምፔሪያሊስት ሞኖፖሎችንና ሽርኮቻቸውን እንጂ የሶስተኛውን አለም ህዝብ አይደለም።

—በልግስና ስም የሚሰጠው ገንዘብ ልክ በየጊዜው ሲቀንስ በብድር ስም የሚሰጠው እየጨመረ ይሄዳል።የብድሩም ወለድ ከፍ ያለ በመሆኑ በዛሬው ጊዜ እዳውን ለመክፈል ብቻ እንኳ ተበዝባገሩ አለም ከሚያገኘው አዲስ እርዳታ ሁለት ሶስተኛውን መልሶ መስጠት አለበት(7)

## ለ) <u>እድገትን የሚገቱ የውስጥ ሀይሎች</u>

ከፍ ብለን እንዳየነው ኢምፔሪያሊዝም በቀኝ አገዛዝ ሆነ በእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ስም በያዛቸው አገሮች ውስጥ ጊዜ ያተላለፈባቸው፣የእርምጃ እንቅፋት የሆኑ መደቦች፣ስርአቶችና ልምዶች እንዲቆዩ



ያደርጋል።

—በህብረሰባዊ አቋም በኩል የተመለከትነው እንደሆን ካፒታሊዝም–ቀደም የሆኑ (ካፒታሊዝም ከመደርጀቱ በፊት የነበሩት) መደቦችና ሀይሎች በስልጣን ላይ ስላሉ እርምጃን አፍነው ይዘው ቴክኒክ እንዳይስፋፋ ያደርጋሉ።ከላብአደሩ የሚጨምቁትን ሃብት መልሰው እንዲያፈራና እንዲራባ ከማድረግ ይልቅ ለከንቱ ብልጭልጭና መቀናጫ ያጠፉታል።የቀረውንም ወደ ካፒታሊስት አገር ባንኮች ያሸሹታል።ብሄራዊ ሃብት በሚገባ አይከማችም፤ይበከናል።የስራ ጉልበትና የሚያፈራው ሃብት ሁሉ ለእድገት ከማገልገል ይልቅ ባክኖ ይቀራል።ለዚህ ምክንያት የሆኑት ሃይሎችና መደቦች በኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ስለተደገፉ በስልጣን ላይ መቆየት ይችላሉ።ኢምፔሪያሊዝም በነሱ አማካይነት ተበዝባጋር አገሮችን ፀጥ ለጥ አድርጐ፣እድገታቸውን ገትቶ ለመግዛትና ለመበዝበዝ ይችላል።

—በባህልና በልምድ በኩል ደግሞ ብዙ የእድገት እንቅፋቶች ሊኖሩና ሊፈጠሩ ይችላሉ።የጅ ስራን መናቅ፣አላፊነትን መፍራት፣በሳይንስና በቴክኒክ አለመተማመን፣ወዘተ....።እንደዚህ ያሉት አጉል ልምዶች ከህዝቡ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሳይሆኑ በጨቋኙ መደብ ጠቅላላ ርእዮተ አለም ስር እንዲዳብሩ የሚደረጉ ናቸው።

በሚቀጥለው ክፍል የኢትዮጵያን ሁኔታ ለይተን በመመልከት ለኢኮኖሚዋ እድገት እንቅፋት የሚሆኑትን ዋና ዋና ሃይሎች ለመጥቀስ እንሞክር።

## <u>II. ኢትዮጵያ በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም በመያዟ ኢኮኖሚዋ ሊያድግ አይችልም።</u>

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በርሻ ላይ የተመሰረተ የፊውዳል ኢኮኖሚ ሲሆን የኢምፔሪያሊዝም ስር መስደድ ስርአቱን በመጠኑ አዛብቶት እናያለን።

### <u>1ኛ. የእድገት አጭር ታሪክ</u>

ባጭሩ መለስ ብለን የእድገት ታሪካችንን ስንመለከት ራሱ

ን የቻለ የፊውዳል ኢኮኖሚ ከቆመ ብዙ ጊዜ እንዳለፈው እንገነዘባለ
ን።የሃብት እርባታ ዋና መሳሪያ መሬት ሆኖ የሃብት አርቢና አዳባሪ ገበ
ሬ ነው።አራሹ የስራውን ፍሬ በሙሉ ለራሱ እንዳያደርግ የመሬቱ ባለ
ቤት የሆነው ባላባት ተጭኖት ይገኛል።የኢኮኖሚውም አቋም ወደኋላ
የቀረ፤እውቀት የተወሰነ፤የስራ አከፋፈል ዘዴ ያልተስፋፋ፤የኑሮ ደረጃ
ዝቅ ያለ በመሆኑ ፍላጎት «ከእጅ ወደ አፍ መጠን» አያልፍም ነበር።
በዚህ ስርአት ውስጥ አልፎ አልፎ የሚገኙት ነጋዴዎችና እንደ ሸማኔ፤
ቀጥቃጭ፤ሸክላ ሰሪ፤ያሉ የጅ ጥበብ ሰራተኞች በዚህ ኢኮኖሚ ውስጥ
የነበራቸው ቦታ በጣም ዝቅተኛ ነበር። የገበያና የልውውጥ እውቀት በ
ጣም የተወሰነ፤የኑሮ ፍላጎት ሁሉ ራስን በራስ በማስተዳደር ላይ ብቻ
የተመሰረተ ነበር።የባላባቶችም ዘረፋ እንኳ በዚሁ ዝቅተኛ ፍላጎት የ
ተወሰነ ነበር።

ይህ አይነቱ ስርአት ንግድንና ኢንዱስትሪን፤የንግድንና የኢን
ዱስትሪን እውቀት በዝቅተኛ ደረጃ እንዲቀሩ አደረጋቸው፤እንዲህ ያለ
ውን እውቀት ሊያመጡ ይችሉ የነበሩትን የእጅ ሰራተኞችና ጠቢቦች
እጅና እግራቸውን አስሮ በእውቀትና በስራ እንዳይዳብሩ አደረጋቸው።

ይህ ሆኖ ሳለ የኢምፔሪያሊስቶች ገፅ በአገራችን መታየት
ጀመረ።ቀስ በቀስም ይዘዋቸው የመጡት አዲስ ልማዶችና ሸቀጦች በአ
ገራችን አዲስ ልምድና ፍላጎትን ፈጠሩ።በብሄራዊ ሀይል ተመርኩዞ ሊ
መጣ ይችል የነበረውን የኢኮኖሚ ለውጥ በመቅደምና ባጭር በመቀጨ
ት መንሰራራት የጀመረው የባእድ ተፅእኖ የነበረው ስርአት ማንቀዝና
የቆየውን ልማድ ማስረሳት ጀመረ።

እነዚህ ኢምፔሪያሊስት ሀይሎች በቀላሉ ስርአቱ ውስጥ ለ
መግባትና ስር ለመስደድ የቻሉት ስልጣን ላይ ባሉት ባላባታዊ መደቦ
ች አማካይነት ነው።አገራችንን በእጃቸው ለማስገባት በቅድምያ ገዢዎ
ቹን መግዛት ነበረባቸው።ይህንንም በቀላሉ በ19ኛው መቶ አመት መ
ጨረሻ ጀምሮ ሊያከናውኑት ችለዋል።በትንሽ ጊዜ ውስጥ ገዢው መደ
ብ የኢምፔሪያሊስቶች ሸቀጥ ማራገፊያና የስልጣኔአቸው እስረኛ ሆነ።
ፍላጎቱና ምኞቱ የተወሰኑ የነበረው ባላባት አዲስ ፍላጎቶች አደሩበት፤
እነዚህም ባእድ ፍላጎቶች ዋጋቸው ከፍ ያለ በመሆኑ የባላባቱ ወጭ



(ወጪአቸው) በዚያው ልክ ጨመረ።የሀብቱ ምንጭም የጢሰኛው ገበ
ሬ ላብና ጥረት በመሆኑ ባላባቱ ብዝበዛውን በመጨመር ወጭውን ሁሉ
በገበሬው ትከሻ ላይ ጣለ።የፊውዳሉ አቋም ያፈራቸው ስርአቶችና አስተ
ዳደሮች ሳይነኩ፤የገበሬው የስራ ዘዴ ሳይሻሻል፤የግፍሪያው ቴክኒኩም
ሆነ መሳሪያው ሳይለወጥ፤የገበሬው ገቢ ሳይጨምር ለባላባቱ የሚከፈለ
ውን እንዲያሳድግ ተጠየቀ።ግብር በአይነቱም በመጠኑም እየጨመረ
ሄደ።«የዋና ዋና ሰብሎች አመታዊ ጭማሪ 0.4% ብቻ ሲሆን የገበሬው
ወጭ (ግብር፤አስራት፤ልዩ ልዩ ታክስ፤መጋዝ) አመታዊ ጭማሪ ደግሞ
በትንሹ በአመት 10% ሆኖ እናገኘዋለን (8)።» ገበሬው ወደድህነት አ
ዘቅት ወደቀ፤በበሽታና በድንቁርና ታስሮ በይበልጥ መሰቃየት ጀመረ።

ኢምፔሪያሊዝም ስር በመስደዱና የባእድ ሸቀጣ ሸቀጦች
በመግባታቸው ፊውዳሊዝምን ሊያጠፋ ይችል የነበረው ውስጣዊ ሀይል
ቀረቀዘ።ፊውዳሊዝም ከባእድ ሀይል ጋር በጥቅም መተሳሰር ጀመረ።ኢ
ፔሪያሊስት ሀይሎች ፊውዳሊዝምን በመደገፍ ብዝበዛቸውን ሊያከናው
ኑ ቻሉ፤ውስጣዊ በዝባዥ ሀይሎች ደግሞ አቋማቸውን እንደያዙ በባእ
ድ ጉልበት በመመካት ብዝበዛቸውን ለማራዘም እድል ገጠማቸው።በ
ኢትዮጵያ ፊውዳሊዝም አለመነቀሉ፤ኢንዱስትሪንና ንግድን የሚያሳድ
ጉ ብሄራዊ ሃይሎች መጥፋታቸው፤ዘመናዊው የኢኮኖሚ ክፍል በውጭ
ሀይሎች መያዙ በገበሬውና በሰራተኛው ላይ ዘረፋን አስከተለ፤የአገሪቷ
ን ኢኮኖሚ አዛባው፤የኢኮኖሚ እድገት እንዳይኖር ከለከለ።

ይህ አይነት ኢትዮጵያ ዛሬ የምትገኝበት ሁኔታ በመሰረቱ
ከሌሎች ተበዝባዥ አገሮች ያልተለየ ሆኖ እናገኘዋለን።ለእድገቷ እን
ቅፋት የሆኑት የውስጥና የባእድ ሀይሎች በመተጋገዝ አገሪቷን በፖለ
ቲካ ሆነ በኢኮኖሚ የኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ጥገኛ አድርገው፤የውስጠ
ቹም ሆኑ የውጮቹ ያለልክ ይበዘብዙዋታል፤ኢኮኖሚዋን እሴናከለው
እንዳይዳብር ከልክለውታል።

## 2ኛ. <u>የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ አቋምና የእድገት ችግሮች</u>

### ሀ) <u>የእርሻ ኢኮኖሚ በፊውዳል አቋም ስር</u>

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋና ምሰሶ ዛሬም ቢሆን እርሻ መሆኑ ግልፅ ነው።90% የኢትዮጵያ ህዝብ በእርሻ ሲተዳደር ከጠቅላላ ብሄራዊ አመት ገቢ 62% ከእርሻ ፍሬ የሚመነጭ ነው።የሀብት አርቢና አዳባሪ አራሹ ገበሬ ሲሆን ከእርሻ መሬት አብዛኛው በርስትነትም ሆነ በጉልት ወይም በመተዳደሪያ የተያዘው በንጉሳዊ ቤተሰብና በቤተ ክርስትያን ከፍተኛ ሹማምንት፣በመኳንንትና በባላባት ነው።ጭሰኛው ገበሬ ከስራው ፍሬ እስከ 75% ድረስ በመጋገር፣በአስራትና በሌላ ልዩ ልዩ ግዳጅ ለባለርስት ያስረክባል።እንደዚህ ያለው ህብረተሰባዊ አቋም በኢኮኖሚው ላይ ተጨማሪ ልዩ ልዩ ጠንቆች አትርፏል፥-በቴክኖሎጂ በኩል ወደኋላ መቅረትን፣የስራ ፍሬ ዝቅተኝነትን፣የስራ ክፍያ አለመኖርን፣የጅ ስራና የሙያተኝነትን መዳከም፣ግብይትና ልውውጥ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መቅረትን።

እንደዚህ ባለ ሁኔታ እድገት ሊመጣ ይችላልን? ብለን ራሳችንን እንጠይቅ።

በመሰረቱ እድገት ሊመጣ የሚችለው የርባታ ሀይሎች ያፈሩት ፍሬ የኑሮ ፍላጐታቸውን ካረካላቸው በኋላ የሚቀረው ትርፍ ሃብት ለልማት እንዲውል ሲደረግ ነው።የአገራችንን ሁኔታ የተመለከትን እንደሆን እንደዚህ ያለው ለእርባታ ሊውል የሚችል ቀሪ ሀብት አነስተኛ ከመሆኑም በላይ "ሙልጭ" ብሎ የሚገባው ለባላባቶች ነው።ባላባቶቹ ይህን ሀብት እንዲራባ መልሰው ስራ ላይ ከማዋል ይልቅ አዲሱ የባእድ ስልጣኔ ያሳደረባቸውን የቅንጦትና የብልጭልጭ ፍላጐቶች ማርኪያ ያደርጉታል።ቀሪውን ወደ ውጭ አገር ባንኮች ያሸሹታል።ይህም ማለት ከላብአደሩ የሚጨመቀው የስራ ፍሬ ሁሉ ለአገሪቷ ኢኮኖሚ ማዳበሪያ በመዋል ፈንታ ለሃብት አደሩ መንደላቀቂያ ያገለግላል ማለት ነው።የበዝባዦችን ጥቅም ለመጠበቅ የተቋቋመውና በተውጣጣ ሰዎች የሚካሄደው ንጉሰ ነገስት መንግስት በግብር መልክ የሚዘርፈውን ሃብት ፍሬ ቢስ የሆነ ቢሮክራሲውንና የጭቆና ሀይሎችን "ለማጠንከሪያ" ያባክነዋል።

በስልጣን ላይ ያሉት በዝባዥ መደቦች ከሚያባክኑት ሀብት ሌላ የፊውዳሉ አቋም ራሱ የሚወልዳቸው የልማት መሰናክሎችና ወደኋላ ጐታች ልማዶች አሉ።ለምሳሌ በመሬት አያያዝና አከፋፈል በኩል ጥቂት ሰዎች በአስርና በመቶ ጋሻ የሚለካ መሬት ይዘው ሁሉንም በሚገባ ለማሳረስ ባለመቻላቸው ለአንድም ጥቅም ሳይውል ጠፍ ሆኖ እንዲቆይ ያደርጉታል።በተለይ ደግሞ በአገራችን የሚገኘው የሰው ሃይል ብዙው ለእድገት የሚያገለግል ስራ ከመስራት ተወግዶ በከንቱ ጉልበቱ ሲባክን እናየዋለን።ለምሳሌ የሴቶችን ጠቅላላ ሁኔታ ብንመለከት በህብረተሰቡ ውስጥ የተሰጣቸው ቦታ ጥረታቸውንና ድካማቸውን ሁሉ ቤት በመያዝ፣በማድቤት በመስራት፣ልጅ በመውለድና በማሳደግ ወስኖ ከወንድ እኩል ለልማት በሚጠቅም ስራ እንዳይሳተፉ ያግዳቸዋል።በዚህ አንፃር ሁኔታቸው የበላይ መደቦችን በአሽከርነትና በገረድነት ከሚያገለግሉት ሰራተኞች በምንም አይሻልም።በተጨማሪ ደግሞ ፍፁም ስራ ፈቶችንና "ሽፍን" ወይም "ድብቅ" ስራ ፈቶችን ሳንጠቅስ ማለፍ አይገባም።ሁለት አይነት ፍፁም ስራ ፈት አለ፤አንደኛው በሃብቱና በሌላው ስራ የሚኖር ስራ ፈት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የስራ ጉልበቱን የሚገዛው ያጣ፣ቦታ የጠፋለት ችግረኛ ነው።ከመጀመሪያዎቹ ውስጥ ንጉሳዊ ቤተሰቦች ባላባቶችና ታላላቅ የቤተክርስትያን ባለስልጣኖች . . . ይገኛሉ።ከሁለተኞቹ ውስጥ ደግሞ በየከተማው የሚንቀዋለሉት ወጣቶች ይገኙበታል።ድብቅ ስራ ፈትነት የሚባለው የሰራተኛው አቅምና ችሎታ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ሳይውል ለይስሙላ ያህል ወይም በተቋረጠ ሁናቴ የሚሰራ ስራ ነው።ለምሳሌ ያህል ለአንድ የተወሰነ ስራ 10 ሰው ያስፈልግ እንደሆን 20 ሰው ተሰብስቦ ያንንው ስራ ቢሰራ የ10 ሰው ድብቅ ስራ ፈትነት አለ ማለት ነው።ለእንዲህ አይነቱ ስራ ፈትነት በኩርማን መሬት ላይ ተጣብበው የሚኖሩ የገበሬ ቤተሰቦች ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ለ) ቀላል ኢንዱስትሪና ዘመናዊ የኢኮኖሚ ክፍል በባእድ ካፒታል ስር

እርሻ በኢኮኖሚያችን ውስጥ የያዘውን ቦታ ሳይለቅና የፊውዳል ስርአቱም ሳይናጋ ከጥቂት አመታት ጀምሮ አንዳንድ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ተቋቁመው፣የመመላለሻ መስመሮች በመጠኑ ተዘርግተው

ዘመናዊ የንግድ ግንኙነቶች ተከፍተው እናያለን።እነዚህና እነዚህን የ
መሳሰሉት ለውጦች የመጡት የፊውዳል ስርአቱን አውድሞ በተነሳ ብ
ሄራዊ ሀይል ሳይሆን በስልጣን ላይ የቀየው ፊውዳል መደብ ከባእድ ኢ
ምፔሪያሊስቶች ጋር በፈጠረው ግንኙነት መሆኑን ከፍ ብለን ጠቅሰናል።
ይህ ግንኙነት —በሌሎች ተበዝባጋር አገሮች እንደተመለከትነው ሁሉ
—ኢትዮጵያም ውስጥ በብዝበዛ ላይ የተመሰረተ ነው።

አገራችን ውስጥ የሚገኙት ኢንዱስትሪዎችና ሌላውም ዘመ
ናዊ የኢኮኖሚ ክፍል የተቋቋሙት በባእድ ከፒታል ድጋፍ ነው።ራሱ
ን የቻለና የዳበረ ብሄራዊ ቡርገፎዋ መደብ በአገራችን ለማደግ አልቻለ
ምና።በስልጣን ላይ ያለው መደብ ራሱን የቻለ "ዘመናዊ ኢኮኖሚ" ለ
መገንባት ቢሻ ከሁሉ አስቀድሞ በፊውዳል አቋሙ ውስጥ የሚገኙትን
ቅራኔዎች ሁሉ ማጥፋት ይኖርበታል።እንደዚህ ያለውን እርምጃ መው
ሰድ ደግሞ ራሱን ማጥፋት እንደሚሆንበት ያውቃል።ከዚህም የተነሳ
ብሄራዊ የሆነ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት እውቀቱ (know-how)
ብቻ ሳይሆን የሚያንሰው ፍላጎቱም ጭምር ነው።እርግጥ በስልጣን ላይ
ለመቆየትና "አዲስ ልምዶቹንም" ለማርካት ሲል አንዳንድ ቀላል ኢን
ዱስትሪዎችን ማቋቋም፤አንዳንድ የንግድ መደብሮችን መክፈት፤ጦር ሰ
ራዊቱን ማጠንከር... ስለሚኖርበት የባእድ መንግስታትን—ኢምፔሪያ
ሊስቶችን—ይረዱት ዘንድ ይጋብዛል፤ጋብዟልም። "ተጋባጋር እንግዶቻ
ችንም" በሌሎች ተበዝባጋር አገሮች እንደሚያደርጉት ሁሉ ኢትዮጵያ
ን ጥገኛ አድርገው ሃብቷን በሰፊው ከመበዝበዛቸውም በላይ ኢኮኖሚ
ዋም በፍጥነት እንዳያድግ አስረው ያዙት።

—ኢትዮጵያ የኢምፔሪያሊስቶች ጥገኛ ሆናለች ለማለት የሚ
ቻለው በምን አይነት ነው?

አንደኛ በፖለቲካ በኩል በስልጣን ላይ የበሰበሰው የባላባ
ት መደብና በአገሪቷ ላይ የተንሰራፋው የፊውዳል አቋም ተደግፎና ተ
ጠግኖ የቆመው በኢምፔሪያሊስቶች ሃይሎች መሆኑን እናውቃለን።ብ
ሄራዊ በዝባዦችና የውጭ በዝባጋር ሃይሎች በጥቅም በመተሳሰራቸው
ሳይደጋገፉ ሊኖሩ አይችሉም።በባህል፤በትምህርት፤በጦር ሃይል፤ወዘተ...
ኢምፔሪያሊዝም በአገራችን የቱን ያህል እንደገባ እናውቃለን፤እንመለ



ስበትም።

ሁለተኛ ደግሞ በኢኮኖሚ በኩል የተመለከትነው እንደሆ
ን የአገሪቱ ኢንዱስትሪና ዘመናዊ የኢኮኖሚ ክፍል በባእድ ከፒታል
ስር ከመሆኑም በላይ የውጭው ንግድ የሚከሄደው ከነዚሁ በዝባጋር ሃ
ይሎች ጋር ነው።የኢትዮጵያን የውጭ ንግድ ስንመለከት በምንልከው
እቃ ቡና ብቻውን 60% ሲሆን ከዚህም ውስጥ 75% ወደአሜሪካ ነው
የሚላከው።እንደዚህ አይነቱ በአንድ እቃ ላይ የተመሰረተና ከአንድ አ
ገር ጋር የተሳሰረ የንግድ ግንኙነት አይነታዊ የበዝባጋርና የተበዝባጋር ግ
ንኙነት ሲሆን የሚያስከትለውንም ጉዳት ሁሉ ከፍ ብለን በዝርዝር አይ
ተነዋል።በጠቅላላው የአገሪቷን ኢኮኖሚ ቆሞ የሚያስኬደው፤የእድገቱ
ን ፍጥነትና አይነት የሚወስነው በአስመጭው አገር ወይም ጥቂት አገ
ሮች ገበያ ላይ ቡና የሚኖረው ዋጋ ነው ማለት ነው።

—የኢትዮጵያ ሃብት በአገር ወንበዴዎች አማካይነት በኢምፔ
ሪያሊስቶች ይበዘበዛል ለማለት የሚቻለውስ እንዴት ነው?

አንደኛ፤በእኩል የጋራ ጥቅም ላይ ያልተመሰረተ የውጭ ን
ግድ ለተበዝባጋር አገሮች የሚያተርፈውን ጉዳትና ኪሳራ አይተናል።የ
ኢትዮጵያም ሁኔታ የተለየ አይደለም። ኢትዮጵያ በንግድ መልክ ወደ
ምእራብ አገሮች ከምትልከው ሶስት አምስተኛው ቡና ነው ብለናል።የ
ቡናውንም ዋጋ ራሷ ሳትሆን የምትወስነው፤አስመጪው አገር አሜሪካ
ና ግብረአበሮቹ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ናቸው "በነፃ ገበያቸው" ላይ
የሚደለድሉት።እንደምናየውም ከአመት ወደ አመት የዚህ እቃ ዋጋ
እየወደቀ ይሄዳል።በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ከነዚሁ አገሮች የም
ታስመጣቸው የፋብሪካ ሸቀጣ ሸቀጦች ሁሉ ዋጋቸው እየጨመረ ነው
የሚሄደው።ይህ የሚያስከትለውን ኪሳራ አይተናል።እንደዚህ ያለው ሁ
ኔታ ለቡና ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ጥሬ እቃዎችም ተመሳሳይ መልክ ሲኖ
ረው ውጤቱም ያው ነው።

ሁለተኛ፤የባእድ ከፒታል ባገራችን ያቋቋማቸውን ኢንዱስ
ትሪዎች የተመለከትን እንደሆን በትርፍ መልክ በያመቱ ከገራችን የሚ
ወጣውና ወደበዝባጋር አገሮች የሚላከው ገንዘብ ምንኛ ከፍ ያለ እንደሆ
ን እናውቃለን።የወንጅ ስኳር ፋብሪካን ምሳሌ ማስታወስ ይበቃል።"ኡች

"ቢ. ኤ. ኢትዮጵያ" የተባለውን የስኳር ፋብሪካ ለማቋቋም 22,400,000 የኢት. ብር የሚሆን የውጭ ካፒታል ገብቷል።ፋብሪካው ትርፍ መስጠት የጀመረው እ እ አ በ1954 አ ም ሲሆን፤በ1964 አ ም በአንድ አመት ውስጥ ትርፉ 8,000,000 (ስምንት ሚሊዮን) የኢት ብር መሆኑን ራሱ ፋብሪካው የሰጠው ቁጥር ያስረዳል።ከተቋቋመበትና ትርፍ መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ (15 አመት ሙሉ) ያትረፈውን ስንገምት ከውጭ ይዞት የመጣውን ካፒታል በስንት እጥፍ መልሶ በንፁህ ትርፍ ኢትዮጵያን ግለብ ከጀመረ ብዙ ጊዜው እንደሆነ እናያለን።(9) የባእድ ካፒታሊስቶች የሚሰሩት ለጥቅማቸው፤የሚመሩት በትርፋቸው በመሆኑ የሚያቋቁሟቸው ቀላል ፋብሪካዎች ሁሉ ገበያቸውን ለማስፋት የታልፁና በርካሽ የሚገኘውን የስራ ጉልበት ለመበዝበዝ የታቀዱ ሲሆኑ፤ከባድ ኢንዱስትሪዎቹ ደግሞ (የሉም እንጂ!) ጥሬ እቃዎችን ለመበዝበዝ የታቀዱ ናቸው።

ሶስተኛ፤በብድርና በርዳታ ስም ስለሚገባው የውጭ ካፒታል በመጀመሪያው ክፍል የጠቀስነውን በማስታወስ እናልፋዋለን።

—በባእድ ካፒታል ላይ ተመርኩዞ የተቋቋመ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ሊያድግና ሊዳብር አይችልም ለማለት የሚያስችለንስ ምንድነው?

በመጀመሪያ መገንዘብ ያለብን ይህ አይነቱ ዘመናዊ ኢኮኖሚ በአገራችን በ30 አመት ውስጥ (ጠላት ከወጣ ጀምሮ) የደረሰበት ደረጃ ከጠቅላላው ብሄራዊ የስራ ፍሬ አንድ አስረኛ እንኳ እንደማይሞላ ነው።

ሁለተኛ ደግሞ፤እንደዚህ አይነቱ የኢኮኖሚ እድገት የታቀደውና የተገነባው በካፒታሊዝም የአስተዳደግ ስርአት ውስጥ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም ማለት ካፒታሊስት አገሮች በታሪካቸው ባለፉባቸው ልዩ ልዩ የእድገት ደረጃዎች ሁሉ እንድናልፍ ታስቦ የተወጠነ ነው። ስለዚህም በመጀመሪያ ቀላል ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡- ለምሳሌ የጨርቃጨርቅ፤የጫማ፤የመጠጥ፤የምግብ እቃዎች፤ወዘተ.... ። እነዚህ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ከተስፋፉና ከዳበሩ በኋላ ቆይቶ በሁለተኛ የእድገት ዘመን መኪናዎችን የሚያወጣና በጠቅላላውም ከባድ ኢንዱስትሪ እንዲቋቋም ይደረጋል።አሁን ባለንበት ደረጃ በአገራችን ለትርፋቸው የሚሰሩት ካፒታሊስቶች እንዲህ ላለው ከባድ ኢንዱስትሪ ሃብታቸውን አያወጡም፡ምክኒያቱም ይህ አይነቱ እርምጃ አገሪቱን በኢኮኖሚ ራሷን አስችሎ ገበያቸውን እንደሚዘጋባቸውና ጊዜያዊው የአገሪቷ ድክምና ጠባብ ገበያ ደግሞ ጥቅም እንደማይሰጣቸው ያውቃሉና።የመአድን ስራዎችንና ከነሱ ጋር የተያያዙ ከባድ ኢንዱስትሪዎችን ሲያቋቁሙ የአገሪቷን ጥሬ እቃ በዝብዘው ለአገራቸው ፋብሪካዎች ለማቅረብ ነው እንጂ ተበዝባጋርዋ አገር ውስጥ እነዚህ እቃዎች ተጣርተው ለእድገቷ እንዲያገለግሉ አይደለም።

የሆነ ሆኖ "እተባለው" ሁለተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ በስራ ላይ ሊውል የሚችል ሀብት —በነሱ አስተሳሰብ— በጣም መደርጀት አለበት።የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከተው እንዲህ አይነቱ ሃብት መቸውንም ሊዳብርና ሊከማች አይችልም።ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉት፤አንደኛ፡ከፍ ብለን እንዳጠቃለልነው የፊውዳሉን ስርአት ለማጥፋት ይችል የነበረው ራሱን የቻለ ነፃ ብሄራዊ የቡርጋርዋ መደብ በአገራችን ሊዳብር አልቻለም። ያሉት ባለሀብቶች አብዛኛዎቹ የፊውዳሉ መደብ ዲቃላዎች ሲሆኑ ብዙዎቹ ደግሞ ከውጭ ካፒታል ጋር በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው።እነዚህም ለእድገት ሊውል የሚችል ሀብት እንዳይከማች ሲያበክኑ፤ለእድገት እንቅፋት የሚሆነው የፊውዳል ስርአት ደግሞ ሳይነካ እንዲቆይ ያደርጋሉ።ሁለተኛ፤የባእድ ካፒታል የሚገኘውን የስራ ፍሬ ሁሉ በትርፍ መልክ ወደአገሩ ያሸሻል።በሌላ የብዝበዛ መንገዶች ደግሞ የአገሪቷን ሃብት በመዝረፍ ለእድገት የሚሆን ካፒታል እንዳይጠራቀም ጨርሶ ያግደዋል።

በሶስተኛውና በመጨረሻው ክፍል ለእድገት ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች ባጭሩ እንጥቀስ።

## III ለእድገት ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ዋና ዋና ነገሮች

የእድገት ችግሮችን ለማስወገድና ብሄራዊ ኢኮኖሚ እንዲዳብር ለማድረግ፡-

1ኛ. ፊውዳሊዝም ከነዘር ማንዘሩ መውደም፤ደጋግፎ የሚያቆየውና የበላይ ጠባቂው ኢምፔሪያሊዝም ከአገር ገለ መ

ጥፋት አለበት።

2ኛ. ነፃ የሆነና ራሱን የቻለ ብሄራዊ ኢኮኖሚ መቋቋም አለበት።

3ኛ. እንዲህ አይነቱ ኢኮኖሚ ሊቋቋምና በፍጥነት ሊዳብር የሚችለው ተበዝባዥ ህዝብ ስልጣንን በጁ ይዞ 1) የሰፊውን ህዝብ ፍላጐት የሚያረካና ለአገሪቱ ሁኔታ የሚስማማ የኢኮኖሚ ስርአት ሲተልም 2) የሶሽያሊስት ህብረተሰብ አጽምና መሰረት ለመጣልና ለማጠንከር ሲችልና "መሰሪያውም የሶሽያሊስት የልማት ፕላን" ሲሆን ነው።

እነዚህ ሶስት ነጥቦች የተያያዙና የተሳሰሩ ናቸው።ከፍ ብለን በሰፊው እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ ውስጥ የፊውዳል አጽም እስካለ ድረስ ምንም አይነት የኢኮኖሚ እድገትና እርምጃ ሊመጣ አይችልም።ይህ ጊዜውን የጨረሰ ስርአት እስከዛሬም ለመቆየት የቻለው አገራችንን ለበዝባዥ አገሮች አሳልፎ በመስጠት ከነዚህ ሰዎች በሚያገኘው ድጋፍ መሆኑን እናውቃለን።እነዚህ የውስጥና የውጭ የጥፋት ሃይሎች በጥቅም ተሳስረው የአገራችንን የተፈጥሮ ሀብት ሲበዘብዙት፤የላብአደሩን ህዝብ ጥረትና ልፋት ቁጭ ብለው እንደመዥገር ሲመጡት፤ብሄራዊ ኢኮኖሚያችንም እንዳያድግ አፍነው ይዘውት እናያለን።የነዚህ ሁለት ሀይሎች መደምሰስ የአገሪቷን የርባታ ሀይል አዲስ ነፍስ ይዘራበታል፤ሃብቷንም ነፃ ሲያወጣ የሰራተኛውን የስራ ፈቃድ ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደርሰዋል።በጠቅላላው ነፃ የሆነና ራሱን የቻለ ብሄራዊ ኢኮኖሚ እንዲቋቋም ያስችላል።ነፃ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ይቋቋም ማለት ለእድገት በውጭ ካፒታል ላይ ሳንተማመን በራሳችን ሃብት ላይ ብቻ ተመርኩዘን ለመራመድ እንቻል ማለት ነው።ራሱን የቻለ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ይቋቋም ማለት ደግሞ ንግድና የውጭ ግንኙነት ሁሉ ይቅር ሳይሆን ማንኛውም ግንኙነት በእኩልነት መልክና የጋራ ጥቅማችንን ከሚጠብቁልን አገሮች ጋር ብቻ ይካሄድ ማለት ነው።

ስለኢኮኖሚ እድገት ከፍ ብለን በተነጋገርንበት ጊዜ እንዲህ አይነቱን እድገት ሊመጣ የሚያስችለው ለርባታ ሊውል የሚችል የተከማቸ ሃብት ሲኖር ነው ብለናል።በፊውዳል ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ



አይነቱ ሃብት ሊከማች እንደማይችል ጠቅሰናል።ስለዚህም ኢንዱስትሪዎች እንዲቋቋሙና "እንዲስፋፉ" ፊውዳሉ መንግስት ወደባእድ ካፒታል ፊቱን አዙሮ በርዳታና በብድር ስም በሚያገኘው ምፅዋት እስከዛሬ እንደቆየ እናውቃለን።የኢትዮጵያ ላብአደር ህዝብ ይህ የተጫነው ስራፊትና ዋጋ-ቢስ የሆነ የፊውዳል መደብ ከላዩ ላይ ቢነሳለት የስራው ፍሬ ሁሉ ለጥቂቶቹ መሽቀርቀሪያና መብለጭለጪያ መዋሉ ቀርቶ እንዲከማችና ለእድገት እንዲያገለግል ማድረግ ይችላል።የፊውዳሉም ግፈኛ መደብ ተምዘግዝጎ ሲወድቅ የወለዳቸው ፍሬ ቢስ ድርጅቶች፤አስተዳደሮችና ልምዶች ሁሉ ከጠቅላላው ስርአት ጋር አብረው ይወድቃሉ።ከዚህ ሁሉ የሚገኘው ሃብት እየተጠራቀመና በልማት ፕላን እየተመራ ጠቅላላ ኢኮኖሚውን ለማሳደግና ለማዳበር ለሚያስችሉት ክፍሎች ወጭ እንዲሆን ይደረጋል።

ከፍ ብለን እንዳየነው የባእድ ካፒታሊስቶች ለትርፋቸው ብቻ ስለሚሰሩ ገንዘባቸውን አውጥተው ኢንዱስትሪ የሚያቋቁሙት ከፍ ያለ ጥቅም ሲኖራቸው እንጂ ለአገሪቷ ብልፅግና በማሰብ አይደለም። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ውስጥ የህዝቡ ደህንነትና የገበያው ጠባብነት ሊገኝ የሚችለውን ትርፍ በጣም መጠነኛ ስለሚያደርገው እድገትን ሊያፋጥኑ የሚችሉ ከባድ ኢንዱስትሪዎች በባእድ ካፒታል ስር ሊቋቋሙና ሊስፋፉ አይችሉም።የተቋቋሙትና በመጠኑ የተስፋፉት ቀላል ኢንዱስትሪዎች የሃገሪቷን የርባታ ሀይል የማያዳብሩ ናቸው።ለምሳሌ ሞርኮ ውስጥ በቅርቡ የባእድ ካፒታል ትልቅ የተሽከርካሪ መኪናዎች ማገጣጠሚያ ፋብሪካ ለማቋቋም ሲያስብ ይህን አይነቱ ኢንዱስትሪ ለአገሪቷ የኢኮኖሚ እድገት አስፈላጊ ወይም ተቀዳሚ ጠቃሚነት አለው በማለት ሳይሆን ትርፉን በማሰብ የመኪና ገበያ እንዲስፋፋና ላካባቢው አገሮች በይበልጥ እንዲሸጥ በማለት ነው።ለሞርኮ ብሄራዊ ኢኮኖሚ ግን የተሽከርካሪ መኪናዎች የሚገጣጥም ፋብሪካ ከሚቆም ይልቅ የእርሻ መኪና የሚያወጣ ፋብሪካ ቢቆም ከፍ ያለ ጥቅም በሰጠ ነበር።

በሶሽያሊስት የልማት ፕላን የሚመራ ኢኮኖሚ ግን ለትርፉ ሳይሆን ለሰፊው ህዝብ ደህንነትና ለአገሪቱ ጠቅላላ ልማት ስለሚሰራ የሚከማቸውን ለእድገት ሊውል የሚችል ሃብት የርባታ ሀይሎችን ወደ

ሚያዳብሩ ስራዎች ይመራዋል።ይህም ቀላል ኢንዱስትሪ በፍፁም ይቀራ
ል ማለት ሳይሆን በይበልጥ በፈጠነ አኳኋን እንዲያድግ የሚደረገው ከ
ባድ ኢንዱስትሪም ሳይረሳ በልማቱ ፕላን ውስጥ ተገቢ ቦታው ይሰጠዋ
ል ማለት ነው።ለምሳሌ በቁጥር በጭሩ ለማብራራት ያህል ዛሬ በፊውዳ
ል ኢትዮጵያ ጢሰኛ ገበሬ ከሚያፈራው ፍሬ 25% ለግል ፍላጎቱ ገቢ
ሲሆንለት የቀረው 75% ለባለርስት ብላባት መንደላቀቂያ እንደሚገባ
እናውቃለን።ገበሬው በምትደርሰው ድርሻ ራሱንና ቤተሰቡን በህይወት
እንዲቆዩ ለማድረግ ይታገላል።ባለርስት ባላባት ደግሞ የሚዘርፈው የግ
ፍ ሃብት ይዝናናበታል፤ያባክነዋል፤ህዝብን ይጨቁንበታል፤ነገር ግን ለል
ማት በሚገባ አያውለውም።ህዝባዊት ኢትዮጵያ በምትቋቋምበት ጊዜ
ግን ይህ ባላባታዊ መደብ ይወድማል፤ስለዚህም ሲባክን ከነበረው 75%
የስራ ፍሬ አብዛኛው ነፃ ይወጣል ማለት ነው።ይህ ሃብት ሙሉ በሙሉ
ወደ ከባድ ኢንዱስትሪ ወጪ ይሆናል ማለት ሳይሆን፤በመጀመሪያ የሰራ
ተኛውንና የገበሬውን የጋራ ፍላጎት እንዲያረካ ይደረጋል።ይህም የሚ
ያመለክተው እንደ ትምህርት ቤቶችን፤የጤና ጥበቃ ድርጅቶችን፤ወዘተ.
. . ነው።ለምሳሌ ለነዚህና እንደነዚህ ላሉት የጋራ ፍላጎቶች በጠቅላላ
ው እስከ 40 ወይም 50% ድረስ እንኳ ወጭ ቢደረግ የቀረው 60 ወ
ይም 50% ለኢኮኖሚ ጠቅላላ እድገት ማፋጠኛ ሊውል ይችላል ማ
ለት ነው።

በሶሽያሊስት የልማት ፕላን የሚመራ ኢኮኖሚ፤እነዚህንና
እነዚህን የመሳሰሉ የልማት ጥረቶችን ከስራ ላይ በማዋልና በማቀናበር
በትንሽ ጊዜ ውስጥ ሊያድግ ከመቻሉም በላይ ትክክለኛ ህብረተሰባዊ ስ
ርአት በማቆም ስራ ፈት በሰራተኛ፤ባለፀጋ በላብአደር እንዳይጠቀምና የ
ስራ ሀይልም በከንቱ እንዳይባክን ያደርጋል።

---

(1) P. JALEÈ "L'Imperialisme en 1970" - Petite Collection Maspero 49 (Paris 1969) ገፅ 81
(2) P. Jaleé,op. cit. ገፅ 60
(3) Ibid.



(4) P. JALEÈ, op. cit. ገፅ 61
(5) BETTELHEIM, CHARLES፡ "Planification et croissans accéléreè", Petite collection Maspero 5 (Paris 1967) ገፅ 40
(6) JALEÉ, op. cit., ገፅ 82
(7) JALEÈ, op. cit. ገፅ 83
(8) "ታጠቅ" ልዩ ቁጥር –ጥቅምት 1962–ገፅ 15
(9) "Ethiopian Observer" Vol. X, No. 4፣ "Development and Legislation in Ethiopia",Krishna Ahooja

## በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

## <u>አስረኛ ጠቅላላ ጉባኤ</u>

## በበርሊን ከተማ ይደረጋል

ይህ ጉባኤ "ምን አይነት ለውጥ በኢትዮጵያ?" በሚል አርእት በሰሚና ር መልክ ሰፊ ውይይት ያደርጋል።ካለፉት አመታት ይበልጥ አባሎች በ ብዛት እንደሚሳተፉ ተስፋ እናደርጋለን

ይህ አስረኛው ጉባኤያችን ታሪካዊ ጉባኤ እንዲሆንና በጠቅላላው የኢ ትዮጵያ ተማሪዎችን ትግል ወደከፍተኛ ደረጃ እንዲያደርሰው አባሎች ሁሉ ተዘጋጅተው እንዲመጡ እናሳስባለን።

| | |
|---|---|
| የስብሰባው ጊዜ፡— | ከ9.8.70 — 17.8.70 |
| የስብሰባው ቦታ፡— | JUGENGÄSTHAUS or Schreber<br>BERLIN 48(MARIENFELDE)<br>BUCKOWER CHAUSEE 114 |

በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ በቅርንጫፍ ማህበራት በኩል የሚጠየቁትን የአባልነት ግዴታዎች ሁሉ መፈፀም ያስፈልጋል